ከ 2 ሚሊዮን ቅጂ በላይ በመሸጥ
ዓለም አቀፍ ዝናን ያተረፈውና
ፊልም የተቀረጸው መጽሐፍ

ጃኒ

ጽሑፍ፡- በጃኒ ኢሬክሰን
ትርጉም፡- በዐቢይ ደምሴ
እርማት፡- በአምሳለ መላከ ብርሐን
እና
ዘነበ ገብረሐና

ይህን መጽሐፍ
ያለ አሳታሚውና ያለ ደራሲው ፈቃድ
ማባዛት ወይም ማሳተም
በሕግ የተከለከለ ነው።

Originally published in the U.S.A. under the title JONI
Copyright © 1976 by Joni Eareckson and Joe Musser
Grand Rapids, Michigan.

መጽሐፉ በመጀመሪያ በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ በሚገኘው ሚቺጋን ግዛት ውስጥ <<JONI>> በሚል ርእስ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ታትሞ ነበር።

ማውጫ

መግቢያ ገጽ

ምዕራፍ 1 1

ምዕራፍ 2 12

ምዕራፍ 3 19

ምዕራፍ 4 32

ምዕራፍ 5 36

ምዕራፍ 6 41

ምዕራፍ 7 45

ምዕራፍ 8 48

ምዕራፍ 9 51

ምዕራፍ 10 56

ምዕራፍ 11 58

ምዕራፍ 12 62

ምዕራፍ 13 65

ምዕራፍ 14 69

ምዕራፍ 15 71

ምዕራፍ 16 77

በጃኒ መጽሐፍ 25ኛ ዓመት ክብረ በዓል ወቅት 82

መደምደሚያ፡- የጃኒ መጽሐፍ 25ኛ ዓመት ክብረ በዓል 92

ለአካል ጉዳተኞች የሚጠቅሙ መረጃዎች 98

ከእንግዲህ የወንበር ቁራኛ ሆኜ ከመቅረት በስተቀር እነኛ ሽባ ሆነው የቀሩትን እግሮቼን ዳግመኛ ላንቀሳቅሳቸው እንደማልችል ታውቆኛል። ያም ሆኖ ግን እንደ አንዳንድ መሰሎቼ አካለ ስንኩላን ሁሉ እኔም ቢያንስ መኪና የማሽከርከር፥ ምግብ የማብሰልና የምወዳቸውን የማቀፍ ዕድል ይኖረኛል ብዬ ገምቼ ነበር» አዎን እንደነዚያ አልፎ አልፎ እንደማያቸው ቢጤዎቼ ሁሉ እኔም ያለ ምንም ችግር ውኃ ቀድቼ ገላዬን የመለቃለቅ፥ ፀጉሬን የማበጠርና ፊቴን የማላመር ችሎታ ይኖረኛል ስል ተስማምቼ ነበር።

ይሁን እንጂ ይህን መሰሉ ምኞቴ ሁሉ ከንቱ መሆኑን የተረዳሁት ውሎ ካደረ በኋላ ነው። ለካስ በሽባነት የተጠመደው እግሬ ብቻ ሳይሆን ከአንገቴ እስከ እግሬ ያለው መላው አካላቴ ኖሮ እጆቼንም ጭምር የማላወሱ ነገር የማይሞከር ሆነ።

፤ ፤ ፤ ፤ ፤ ፤ ፤ ፤ ፤ ፤ ፤ ፤ ፤ ፤

እናም በዚያን ጊዜ ነበር ወደ እግዚአብሔር አምርሬ መጮኽ የጀመርኩት። «ለመሆኑ የፈጠርከኝ ለዚህ መሰሉ ፍዳና ሥቃይ ልትዳርገኝ ኖሯል እንዴ?»

፤ ፤ ፤ ፤ ፤ ፤ ፤ ፤ ፤ ፤ ፤ ፤

ጃኒ ላልታሰበ አደጋ ተጋልጣ መላው አካሏ ሽባ ቢሆንም ከቀጣዩ ትረካ እንደምንረዳው ቀሪውን ሕይወቷን ላለማጨለም በብርቱ ስትታገልና ስትፍጨረጨር እናያለን። እነኛ በአደጋው ሳቢያ የከነቸሩ ጣቶቿ እጥፍ ዘርጋ ማለት ተስኗቸው እንደተቆለመሙ ቢቀሩም እንኳ ጃኒ በጥርሶቿ ብሩሽ ይዛ በመሳልና ብዕር ይዛ በመጻፍ ዓለም አቀፍ ዝናንና እውቅናን ስታተርፍ እንመለከታለን። ከዚህ የምንረዳው ትልቅ ቁም ነገር እግዚአብሔር ከልብ ላመኑበትና በንስሐ ለሚሹት ሁሉ የቱን ያህል የቅርብ ረዳትና አለኝታ እንደሆነ ነው።

ይህ የጃኒን ታሪክ ያዘለው መጽሐፍ በሚሊዮን ቅጂዎች ከመሸጡም በላይ በታላቅ ፊልምነት በመቀረጹ በመላው ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያኖች መጽናኛና መበረታቻ ሆኗል። እርስዎም ከዚህ መሰሉ በረከት ይቋደሱ ዘንድ በንባቡ ይግፉበት!

መግቢያ

እስቲ አንዲትን ደቂቃ ብቻዋን ነጥለን በመውሰድ የቱን ያህል ረጅም እንደሆነች እናጢን ወይም እናሰላስል! ያለጥርጥር ያቺ ደቂቃ ምንም ሳይታወቀን ነው ከመቅፅበት ተፈትልካ የምታልፈው። እንግዲህ ይህን መሰሎቹ 60 ደቂቃዎች ናቸው በአንድ ሰዓት ውስጥ የሚያጋጥሙን። በቀን ውስጥ ደግሞ ቁጥራቸው ወደ 1440 ያድጋል ማለት ነው። እናም በዚህ ስሌት መሠረት እኔ በ17 ዓመት ዕድሜዬ ውስጥ ያሳለፍኳቸው ወይም የኖርኳቸው ደቂቃዎች ብዛት 9,000,000 ነው ማለት ነው።

ይሁን እንጂ አንባቢዎቼ ከልብ እንዲያጤኑልኝ የምሻው ነገር ቢኖር ያቺ ኢምንት ተብላ የተናቀቸው አንዲት ደቂቃ የቱን ያህል የፍጡራንን የወደፊት ዕድልም ሆነ ሕይወት የመወሰን ብቃት እጎዳላት ነው። እነሆ እኔ በእድሜዬ በብዙ ሚሊዬን የሚቆጠሩ ደቂቃዎችን ባሳልፍም በአንዲት ደቂቃ ውስጥ ባሉት 60 ሴኮንዶች ፍጥነት ነበር ሕይወቴ ሊለዋወጥ የቻለው። እናም በዚያን መሰሉ እድሜዬ ያሳለፍኩት የፍቅር ሕይወት፥ የነበረኝ ማኅበራዊ ተሳትፎ፥ ያካበትኩት ልምድና ዕውቀት ብሎም ያውጠነጠንኩት ዕቅድና መሰናዶ ሁሉ በሐምሌ 30 ቀን 1967 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) በተከሰተ የደቂቃ ገጠመኝ ሟሽሾና ተኮላሽቶ ቀረ።

አውቁ ደራሲ ኦስኮር ዋይልድ በአንድ ወቅት ሲጽፍ «በሕይወት ዘመናችን ውስጥ ለጎዘን ሊያጋልጡን የሚችሉ ነገሮች ሁለት ብቻ ናቸው። አንዱ የምንፈልገውን ነገር ያለማግኘታችን ሲሆን፥ ሌላው ደግሞ የምንፈልገውን ሁሉ የማግኘታችን ሁኔታ ነው» ማለቱ ትዝ ይለኛል።

እነሆ እኔም ከእርሱ መሠረተ አሳብ በተቃራኒው በመንደርደር በሕይወት ዘመናችን ውስጥ ለደስታ ሊዳርጉን የሚችሉት ሁለት ሁኔታዎች ብቻ ናቸው፤ አንዱ እግዚአብሔር የምንለውን ሁሉ ሲሰጠን ሲሆን፥ ሌላው ደግሞ በጭራሽ ሊከለከለን ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሻለሁ። ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ማወቅ ብቻ ሳይሆን ኃላፊውም ሆነ መጪው ጊዜ ይታየዋልና የሚያደርግልን ሁሉ የሚጠቅመንን ነው። በእርሱ ቸርነትና ቅንነት ፍፁም ልንተማመን ይገባል። እናም የቱንም ያህል መከራና ሥቃይ ቢደርስብንም ዳሩ ግን ለበጎ መሆኑን አውቀን መጽናናት አለብን።

ጃኒ ኢሬክሰን

«በሁሉ እንገፋለን እንጂ አንጨነቅም፤ እናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም፤ እንሰደዳለን እንጂ አንጣልም፤ እንወድቃለን እንጂ አንጠፋም፤ የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሥጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁልጊዜ የኢየሱስን መሞት በሥጋችን ተሸክመን እንዞራለን። . . . በብዙዎች በኩል የተትረፈረፈው ጸጋ ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋናን ያበዛ ዘንድ፥ ሁሉ ስለ እናንተ ነውና። ስለዚህም አንታክትም፥ ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል።» (2ኛ ቆሮንቶስ 4፡8–10፤ 15–16)።

ምዕራፍ አንድ

በስተምዕራብ ማሽቆልቆል የጀመረችው የሐምሌ ጀንበር አሁንም የቼሳፕኪን ባህረ ሠላጤ እንዳንጸባረቀችው ናት፤ እኔም ተንደርድሬ በመዝለል ከዚያ ከቀዝቃዛ ባህር ውስጥ በግንባሬ ስጠልቅ ለጊዜውም ቢሆን ደስታና እርካታ የተሰማኝ ለመሆኑ አይዘነጋኝም። ዳሩ ግን በዚያው ቅፅበት አናቴ ከባህሩ ወለል ጋር ተላትሞ ኖሮ ልክ ኤሌክትሪክ እንደያዘው ሰው የጆሮ ግንዴ መርገብገብ፥ የደም ሥሬ ተወጣጥሮ መንዘርና በማብቂያውም የሰውነቴ ተዝለፍልፎ መዘረጋጋት አይረሳኝም። ያም ሆኖ ግን ሙሉ በሙሉ አቅሌን በመሳቴ አሸዋው ላይ በአፍንጫዬ ተደፍቼ መተኛቴ የሚዘነጋኝ አይደለም።

ታዲያ በዚያን ጊዜ በመጠኑም ቢሆን ግራ ያጋባኝ ከደረቴ እንደተጣበቁ የቀሩት እጆቼና በአሸዋው ላይ ተወናከረው የማይላወሱት እግሮቼ ጉዳይ ነበር። ወዲህ ብል ወዲያ ነቅነቅም አልል ስላልኩኝ ምናልባት እዚሁ ባህር ውስጥ እንደተጋደምኩ ልቀር ነው እንዴ? በማለት መሥጋት ጀመርኩ።

ወዲያውኑ ደግሞ ዙሪያዬን የከበበኝ ባህር እንደመናወጥ ብሎ ለጥቂት ደቂቃ ያህል ካንሳፈፈኝ በኋላ ተመልሼ ከአሸዋው ላይ ተዘረጋሁ። የአሁኑ ፍርሃቴ ግን ለየት ያለ ነበር። ድንገት ለዓሣ ማጥመጃ ከተወረወረ መረብ ውስጥ ገብቼ ተተብትቤ ይሆናል ስል ባለ በሌለ ኃይሌ ለመንፈራገጥ ሞከርኩኝ፤ ይሁን እንጂ እጄና እግሬ ቅንጣት ያህል አልላወስ አሉኝ። ምን ነካኝ ይሆን? እርግጥ ከባህሩ ወለል ላይ ወርጄ የተላተምኩት በአፍንጫዬ በመሆኑ በራስ ቅሌ ላይ ጉዳት ደርሶ ሊሆን ይችላል ብዬ አሰብኩ። ደግሞ በአስተላሰቤ ላይ ያስከተለው አንዳችም ተጽዕኖ አልነበረም፤ ምክንያቱም ወደዚያ ባህረ ሠላጤ መቼና ከነማ ጋር እንደመጣሁ፤ ምን ስሠራ እንደዋልኩና በመጨረሻም እንዴት ባህሩ ውስጥ በጭንቅላቴ ተወርውሬ እንደገባሁ ጭምር ስለሚታወሰኝ ነው።

ታዲያ ምን ነካኝ? ወይ እኔ ልጄት! እንዳው ከቤቴ በሰላም ወጥቼ የባህር እራት ሆኜ ልቀር ነው? ሳንባዬ የአየር ያለህ እያለ እያስጨነቀኝ ነው! የእኔ ነገር በቃ አከተመለት ማለት ይሆን? ለዚያውም ውኃ ተግቼ ልሞት! ኧረ ተው አምላኬ እርዳኝ! እባክህን አንዴ እንኳን እንደ ልቤ ተንፍሼ እንድሞት ከዚህ መቀራቅርት ውስጥ መንጭቀህ አውጣኝ! ከዚህ ጭንቅና ጣር ገላግለኝ! .....

ልክ በዚያኑ ቅፅበት ነበር «ጃኒ» የሚል የተድፎነፎነ ድምጽ በርቀት የተሰማኝ። ድምጹ ስሜን በመደጋገም እየተጣራ ሲቀርብኝ ግን

የእጎቴ የካቲ መሆኑን በመለየት በሆዴ «ተመስገን አምላኬ!» ስል ምስጋና አቀረብኩ። ካቲ አጠገቤ ደርሳ ከዛ ከተዘረርኩበት እንደ ምንም ተፍጨርጭራ ካነሣችኝ በኋላ ባለ በሌለ ኃይሏ እየገፋች ወደ ላይ አወጣችኝ። እኔም ያንን የነመጀሁለትን አየር በረጅሙ እየማግሁ ትንፋሼ መለስ ከማለቱ ነበር ካቲ በአቅራቢያችን አንዲት ጀልባ በመቅዘፍ ላይ ላለ ሰው በልመና እጆቿን እያርገበገበች የተጣራችው። ሰውዬውም ከአጠገባችን ደርሶ ተጋግዘው ከጀልባው ላይ ካወጡኝ በኋላ ወደ ባህሩ ዳርቻ ወሰዱኝ። በዚያን ጊዜ ነበር «ከሞት ስለዳንኩኝ ክብር ምስጋና ይግባህ አምላኬ!» ስል ለሁለተኛ ጊዜ በሆዴ ጸሎት ያደረስኩት።

ታዲያ ከዚያ ከፈራሁት ሞት ላምልጥ እንጂ ከጀልባዋ መውረድ አልተቻለኝም ነበር። ካቲና ባለ ጀልባው ዱብ ዱብ እያሉ ቢወርዱም እኔ ግን እጄም ሆነ እግሬ አልታዘዘም ብሎኝ በዚያው በተጋደምኩበት ተዘርሬ ቀረሁ። ያን ጊዜ ለሁለት የሳንሳ በመሸከም አውርደው ከአሸዋው ላይ አሳረፉኝ። በባህሩም ዳርቻ በመዝናናት ላይ የነበረው ሕዝብ ምን ጉድ ተፈጠረ ሲል እየተሯሯጠ በመምጣት ከብቦ ያየኝ ጀመር። ጩኸቱና ግርግሩም በዚያኑ መጠን በመጨመሩ ሆድ መባስ ብቻ ሳይሆን ጭንቀትም ስለወረረኝ «እባክሽን ካቲ ከአጠገቤ ዘወር እንዲሉ አድርጊልኝ» ስል ተማጠንኳት።

እንደ አጋጣሚ የካቲ እጮኛ የሆነው ባች በዚያን ጊዜ አጠገባችን ደርሶ ኖሮ «አዎን! ንፋስ እንድታገኝ ራቅ ራቅ በሉላት እንጂ!» እያለ ሰዎችን ከገፋ በኋላ ከጎኔ ተንበርክኮ «ተረፍሽ አይደል ጄኒ? አይዞሽ ከእንግዲህ ምንም ነገር አትሆኚም!» ሲል ሊያበረታታኝ ሞከረ።

«ምኑን ተረፍኩት ብለህ ነው ባች? መንቀሳቀስ እንኳን አልቻልኩም እኮ!» ብዬ ከመለስኩለት በኋላ ወደ ካቲ እያየሁ «እስቲ ነይና እጆቼን ይዘሽ ቀና አድርጊልኝ» ስል ለመንኳት።

ካቲም ወዲያውኑ በርከክ ብላ «ይኸው ቀና አድርጌሻለሁ» አለችኝ ፈገግ እያለች። «እንዴ እጆቼን ይዘሽ ነው ያነሣሽኝ ማለት ነው?» ስል በድጋሜ ጠየኳት «አዎ እጆችሽን ይዤ ነው ያነሣሁሽ፤ ምን ነው ስጎትትሽ አንጓው ላይ እንኳን አልተሰማሽም እንዴ?» አለችኝ ካቲ በጥያቄዬ ግራ እንደመጋባት ብሏት።

«የለም አልተሰማኝም! እስቲ ጣቶቼን ጭምቅ አድርጊና ያዢያቸው።»

ካቲ ይኸው አለችና ጎንበስ አለች። ጥቂት ቆይታም ቀና በማለት «እና አሁንም ጣቶችሽን ስጎትት አልተሰማሽም?» ስትል በመገረም ጠየቀችኝ።

«አልተሰማኝም!»

«ቆይ እስቲ!» አለችና አሁንም ወደ እግሮቼ ወረድ በማለት «አሁንስ ጭንና ተረከዝሽን ስነካካው ምንም አልተሰማሽም?» ስትል በድጋሚ ጠየቀችኝ።

«ምንም አልተሰማኝም!»

«ወይኔ እጎቴን!» ብላ ብድግ አለች። በኋላ ትከሻዬን ጭምድድ አድርጋ በመያዝ «እዚህም ላይ ምንም አይሰማሽም?» አለችኝ ተስፋ በቆረጠ አንደበት።

«ትከሻዬን የነካሽኝ ለመሆኑ እንኳን ታውቆኛል» አልኳት ፈገግ እያልኩ።

እርሷም በዚች ትንሽ ፍንጭ ሌላው ሙሉ በሙሉ በድን ላለመሆኑ በመተማመን ጭንቀቷ እየለቀቃት «አይዞሽ ጃኒ፥ አንዴ ሀኪም ቤት እንድረስ እንጂ ወዲያውኑ ነው እጅና እግርሽን የሚያፍታቱልሽ» ስትል በፈገግታ ተፍነከነከች።

ወዲያውኑም የአምቡላንስ ድምጽ ተሰምቶ ብዙም ሳይቆይ መኪናው ደረሰ። ነጫጭ ልብስ የለበሱት የጤና ረዳቶችም ዱብ ዱብ ብለው በመውረድ ሕዝቡን ገለል ካደረጉ በኋላ በመቻኮል ከሸራ አልጋ ላይ አስተኝተው ወደ አምቡላንሱ አስገቡኝ፤ ካቲም በባች መኪና እንደምትከተለኝ ነግራኝ ተለየችኝ።

አምብላንሱ ጡሩምባውን በረጅሙ ለቅቆ ተፈተለከ። ታዲያ ለጥቂት ደቂቃዎች ከተጓዝን በኋላ ነበር አጠገቤ ተቀምጦ ወደ ነበረው የጤና ረዳት መልከት በማለት ለቀላል ነገር ይህን ያህል ስላስቸገርኳችሁ አዝናለሁ። እርግጠኛ ነኝ ይህ ሰውነቴን የወረረው ድንዘዛ አንድ ሁለት መርፌ ከተወጋሁ በኋላ ድራሹ እንደሚጠፋ ስል ፈገግ እያልኩ ላዋራው ሞከርኩ። እርሱ ግን መልስ በመስጠት ምትክ ከፌቴ ላይ ተመርጎ የነበረውን አሸዋ አራገፈልኝና ዝም ማለቱን መረጠ። ታዲያ በዚህ ዝምታው ሰውየውን መታዘቤ አልቀረም። ምክንያቱም አንዴ ሆስፒታል ደርሰን ሐኪሞቹ እንደነገሩ ካዩኝ በኋላ ወደ ቤቴ እንድመለስ እንደሚፈቅዱልኝ እርግጠኛ በመሆኔ ነው። እናም ያንን የጤና ረዳት ለማዋራት ከመሞከር ይልቅ በጥሩንባው ጩሀት ሳቢያ ተደናግጦ በየመንገዱ ወደ ቆመው ሕዝብ በመስኮት

አያጮለግኩ መመልከቱን ተያያዝኩት። ያም ሆኖ ግን ጣልቃ እያስገባሁ አምላኬን መማጸንና ማመስገኑን አልረሳሁትም ነበር።

በመንገዱ ግራና ቀኝ ብዙ ሕዝብ ቆሞ ሳይ፡ . . . . . .

እግዚአብሔር እረኛዬ ነው።

ብዬ እንደሆን አምቡላንሱን መብራት ሲያስቆመው ደግሞ. . . . .

የሚያሳጣኝም የለም

እልና እቀጥላለሁ። እንደዚሁ ፍጥነት ሲጨምር. . . . . .

በለመለመ መስክ ያሳድረኛል

እላለሁ። ጠመዝማዛ ላይ ደርሶ በረድ ሲል. . . . . .

ነፍሴን መለሳት

በማለት አረፍ እላለሁ። ከዚያም በመቀጠል. . . . . .

ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ።

ብዬ በአሳብ ጭልጥ ብዬ እሄዳለሁ። ታዲያ.. .. ....

በሞት ጥላ መካከል እንኳን ብሄድ፤

አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤

በማለት ላይ እንዳለሁ ነበር አምቡላንሱ [ለድንገተኛ ሕሙማን ብቻ የተፈቀደ] ከሚለው ሕንጻ ሥር ደርሶ የቆመው በዚህን ጊዜ ከተማው ድንግዝግዝ ብሎ ጨልሞ ነበር።

ወደ ድንገተኛ ሕሙማን መስተናገጃው ክፍል እንደገባን ያጤንኩት ነገር ቢኖር የቱን ያህል የተጣበበና የተጨናነቀ እንደነበረ ነው። እኔንም ወዲያውኑ ከአንድ ተሽከርካሪ ጠረጴዛ ላይ በማስተኛት ወደ አንዲት አነስ ያለች ክፍል ውስጥ ወሰዱኝ። ያችም ክፍል ብትሆን ዙሪያዋን በተለያዩ የመድኃኒት ጠርሙሶች፥ ብልቃጦች፥ ሣህንና ትሪዎች፥ መቀሶችና ወረንጦዎች . . . ወዘተ የተሞላች ነበረች። አየሩም በተለያዩ ጸረ ተዋሲያን ቅመማ ቅመሞችና በአልኮል ሽታ ተመርዟል።

ብዙም ሳይቆይ ነበር አንዲት አስታማሚ ወደ እኔ በመቅረብ ወዲያ ወዲህ እንዳልላወስ ከጠረጴዛው ጋር በቀበቶ ጠርንቃ ያሰረችኝ። እኔም በአድራጎቷ ግራ በመጋባት እንዳቅሜ ለመንፈራገጥና ተቃውሞዬን ለማሳየት ሞክሬ ነበር። ሆኖም ግን እጆቼንም ሆነ እግሮቼን ቀና ላደረጋቸው እንኳን አልቻልኩም ነበር። በዚያን ጊዜ ደግሞ ካቲ

አጠገቤ ባለመኖሯ ተስፋ ቆርጬ እንባዬ በዓይኖቼ ተንቆረዘዘ። ሆኖም ግን እራሴን በራሴ በማጽናናት ወደ አስታማሚዋ ቀና ብዬ አየሁና «እባክሽን ምን እንደሆንኩ ብትነግሪኝ? ስል ለመንኳት።

አስታማሚዋ ግን ለጥያቄዬ ቀጥተኛ መልስ በመስጠት ምትክ ከጣቴ ላይ የነበረውን ቀለበት እያወለቀች፤ «የሚመረምርሽ ሐኪም በመምጣት ላይ ስለሆነ የአሁኑን ጥያቄሽን ለእርሱ ልታቀርቢለት ትችያለሽ። በተረፈ ግን የሐኪም ቤቱ ደንብ ነውና ማንኛውንም ጌጣጌጦችሽን በማውለቅ በዚህ ፖስታ ውስጥ አሽጌ ማስቀመጥ አለብኝ» አለችኝ።

ግን እዚህ ለምን ያህል ጊዜ የምቆይ ይመስልሻል? አልኳት አሁንም በማስተዛዘን።

«ይቅርታ ወይዘሪት እንዲህ ያለውን ጥያቄ ሊመልስልሽ የሚችለው ሐኪሙ ብቻ ስለሆነ ቅድም እንደነገርኩሽ እርሱን ብትጠይቂው ይሻላል» አለችኝ እንደ መኮሳተር ብላ።

ወዲያውኑ ደግሞ አንዲት ሌላ አስታማሚ በእጆቿ ብዕርና የሚሞላ ቅጽ ይዛ ወደ እኔ በመቅረብ ስምሽን ብትነግሪኝ» አለችኝ

ጃኒ ኢሬክሰን

«ጆኒ አልሽኝ» ግን የምትጽፊው ጄ-ኦ-ኤች-ኤን-ዋይ ብለሽ ነው?» አለችኝ አስታማሚዋ ለመጻፍ ብዕሯን እያመቻቸች።

«ጄ-ኦ-ኤን-አይ ብዬ ነው የምጽፈው።»

«ኤሪክሰንንስ?» አለችኝ አሁንም።

በቅድሚያ የአባቴ ትክክለኛ ስም ኤሪክሰን ሳይሆን ኢሬክሰን ነው። የሚጻፈውም ኢ-ኤ-አር-ኢ-ሲ-ኬ-ኤስ-ኦ-ን ተብሎ ነው እንደመሰላቸት ብዬ።

«እድሜሽ?»

እድሜዬ 17 ነው።

«የተወለድሽበትን ዕለት፥ ዓመተ ምሕረትና ስፍራ ብትነግሪኝ?»

ይህን የመሳሰለውን ነገር አሁን በትክክል ለማስታወስ አልችልም። ስለዚህ ካቲ የምትባለውን እኅቴን ውጪ ልታገኚያት ስለምትችዪ ለምን እርሷን አትጠይቂያትም?

አስታማሚዋ በዚህ መልስ አሰጣጤ እንደመናደድ ብላ መጠይቁን በማፋጠን ከክፍሉ ውልቅ ብላ ወጣች። ያቺ የቀድሞዋ አስታማሚ ግን

ጌጣ ጌጤን ያስቀመጠችበትን ፖስታ አንሥታ ከትራስጌዬ ከነበረች አንዲት ቁም ሳጥን ውስጥ ከከተተች በኋላ ወደ ሕክምና ዕቃዎቿ መደርደሪያ በመሔድ አንድ ሹል መቀስ ይዛ ተመለሰች

እኔም በነገሩ በመደናገጥ «እንዴ መቀሱ ደግሞ ምን ያደርግልሻል?» ስል ጠየቅኳት።

እርሷም ሳቅ እንደማለት ብላ «ይህን የለበስሽውን የዋና ቡታንታ ቆርጬ ለማውጣት ነው» ስትል መለሰችልኝ።

«ዲስ ሙታንታ እኮ ነው/ ብታምኝም ባታምኝም ገና ዛሬ ነው የለበስኩት ስለዚህ ምን አለ. . . . . .

«ይቅርታ የእኔ እኅት! ይሄ የሆስፒታሉ ደንብ ስለሆነ እንደታዘዝኩት መፈጸም አለብኝ» ብላ በግራና በቀኝ ከተረተረችው በኋላ አውልቅ ከቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ ከተተችው።

ከዚያም አንድ አንሶላ አምጥታ ካለበሰችኝ በኋላ ወደ ሌላው ሥራዋ ተመለሰች። ይህን ይህን ሳይ ነበር የደረሰብኝ ጉዳት ቀላል አለመሆኑን የተረዳሁት። ማምሻውን ወደ ቤቴ የመመለስ ጉጉቴም የሚሸሸው ከዚያ በኋላ ነበር። አንሶላው ተንሸራቶ ደረቴና ጡቴ እርቃኑን ቢቀርም ዳሩ ግን እጆቼን ማላወስ ባለመቻሌ ልሸፍነው እንኳን አልቻልኩም። አስታማሚዋንም አልብሺኝ ስል በድጋሚ ላስቸግራት አልፈለግኩም። በዚያን ምትክ ወደ ጣሪያው አንጋጥጬ እግዚአብሔርን በጸሎቴ መነዝነዝ መረጥኩ።

«በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ

አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤. . . . . »

በሌላ በኩል ደግሞ አደጋ ላይ መውደቄን ወላጆቼ ሲሰሙ ምን እንደሚውጣቸው እየታሰበኝ እንባዬን መቆጣጠር ተስኖኝ ነበር። ያም የምወደውና የሚወደኝ ፍቅረኛዬ ዲክ በዚህ ዜና ሳቢያ የሚያድርበት ድንጋጤ እየታየኝ በአሳብ መጨነቄ አልቀረም። እንግዲህ አስተሳሰቤ በዚህ መልኩ በተበታተነበት ጊዜ ነበር አንድ ረዘም ያለና ነጭ ጉርድ ካፖርት የለበሰ ሰው ወደዚያች ክፍል የገባው።

ሰውየው ፈገግታ በተላበሰ እይታ ጎንበስ ብሎ እጅ ከነሳኝ በኋላ

«ዶክተር ሼሪል እባላለሁ የአንቺስ ስም ማን ነው? ሲል ጠየቀኝ።

ጃኒ አልኩት እኔም በተራዬ ፈገግ ለማለት እየቃጣሁ።

«እስቲ ምን እንደነካሽ ልይ» ብሎ ወደ ካፖርቱ ኪስ እጁን በመክተት ላይ እንዳለ እኔ ግን አሁንም አላስችል ብሎኝ እባክህን ዶክተር መቼ ነው ወደ ቤቴ የምመለሰው? ስል ጠየኩት።

«ቆይ ትንሽ ታገሺኝ!» ሲል ዶክተሩ መልሶልኝ፤ ከኪሱ የወጣውን ረጂም መርፌ ይዞ ወደ ግርጌዬ ዝቅ ካለ በኋላ

«አሁን እግርሽን በመርፌ መውጋቴ አልተሰማሽም?» በማለት ጠየቀኝ።

እኔም «ምንም አልተሰማኝም» ስል መለስኩለት።

«አሁንስ?» አለ መርፌውን ይዞ ወደ ባቴ ላይ ከፍ ካለ በኋላ።

«አሁንም የተሰማኝ ነገር የለም» አልኩት ከንፈሬን በንዴት እየነከስኩ።

ዶክተሩ ካጎነበሰበት ቀና ብሎ የቀኝ ከንዴን አንሥቶ ከያዘ በኋላ ከብብቴ ስር እስከ ጥፍሮቼ ጫፍ ድረስ ተራ በተራ በመርፌው እየወጋ የተሰማኝ ነገር እንዳለና እንደሌለ ጠየቀኝ። እኔም በተከታታይ በአሉታ መለስኩለት። እርሱም መልሶ ከጎኔ ካሳረፈ በኋላ ተስፋ ባለመቁረጥ ከትከሻዬ ላይ ከፍ አለና መርፌውን ወጋኝ።

በዚያን ጊዜ ግን የመርፌው ቆዳዬን በስቶ መግባት ተሰምቶኝ «አሁን እንደወጋኝ ተሰምቶኛል» ስል ትንፋሼ ቁርጥ ቁርጥ እያለ መለስኩለት።

«በጣም ጥሩ» አለና ዶክተሩ በማስታወሻ ደብተሩ ላይ አንዳንድ ነገሮች መጻፍ ጀመረ። ዳሩ ግን በዚያ መሀል ሌሎች ሐኪሞች ወደ ክፍሉ ውስጥ በመግባታቸው ዶክተር ሼሪል መጻፉን አቁሞ ለጥቂት ጊዜ ያህል ከእነርሱ ጋር ሲወያይ ቆየ። በመጨረሻም ያንን እኔን ሲወጋበት የቆየውን መርፌ አንሥቶ ለሌላው ሐኪም ሰጠው። ይሄኛውም ሐኪም ከቀድሞው በተመሳሳይ ሁኔታ የተለያየውን የሰውነቴን ክፍል ከጠቀጠቀ በኋላ ወደ ዶክተር ሼሪል ጠጋ በማለት «የአከርካሪ አጥንቷ መናጋት ነው» አለ።

«አዎን! የእኔም ግምት እንደዚያው ነው። ችግሩ በአራተኛውና በአምስተኛው ደንደሶቿ መለያየት ሳቢያ ይመስለኛል።»

«ጥሩ በዚህ እስከተስማማን ኤክስሬይ ብትነሣም ባትነሣም የሚኖረው ጠቀሜታ የለም። ስለዚህ ያለን አማራጭ በቀጥታ የአከርካሪ አጥንቷን በሚቆጣጠረው የአእምሮዋ ክፍል ላይ ይሆናል። ስለዚህ ረዳቶችህ አስፈላጊውን ቅድመ-ዝግጅት አሁኑኑ

እንዲያጠናቅቁ አድርግ» ብሎ ከክፍሉ ወጣ። ዶክተር ሼሪልም በተራው ለአስታማሚዎቹ አንዳንድ ትእዛዝ ከሰጠ በኋላ ተከታትሎት ወጣ። ታዲያ የዶክተሮቹ ቋንቋ ሙሉ በሙሉ ባይገባኝም እንኳ የሚያደርጉትን ሁሉ አንድ በአንድ እየተከታተልኩ ነበር። በቅድሚያ አንዱ አስታማሚ ከንዴን በጥጥ ከጠራረገች በኋላ አንድ መርፌ ከደም ሥሬ ውስጥ በመሰካት የመድኃኒቱ ብልቃጥ እስከሚንጠፈጠፍ ቆማ ስትጠብቅ ቆየች። ሌላዋ አስታማሚ ደግሞ በተራዋ ጥቂት ቆይታ የፀጉር ቶንዶስ ይዛ ቀረበችኝ። በዚህን ጊዜ ነበር በንዴትና በድንጋጤ ተውጬ አይደረግም! በምንም ሁኔታ ፀጉሬን አትቆርጡትም! ስል መጮህ የጀመርኩት። ይሁን እንጂ የምከላከልበት ምንም አቅም ስላልነበረኝ ያንን የምኮራበትንና የምመካበትን ወርቃማ ፀጉሬን እየነመዱ ከፊቴ ይከምሩት ጀመር። ይህም አንሶ ደግሞ ሌላኛይቱ አስታማሚ በሌላ ሣህን ውስጥ የሳሙና አረፋ ይዛ ስትመጣ አየኋት። ማለትም ፀጉሬን በቶንዶስ ማንሣት ብቻ ሳይሆን የራስ ቅሌን ጭምር በስለት ሊላጩት ነው። ይህን መሰሉ ቅድመ ዝግጅት ለቀጣዩ ከባድ እርምጃ ምልክት መሆኑን በማጤን አሁንም አምላኬን እርዳኝ ስል በሆዴ መጨቃጨቁን ገፋሁበት። በዚህ መሰሉ የአእምሮ ነውጥ ላይ እንዳለሁ ነበር አሁንም ዶክተር ሼሪል ወደ ክፍሌ ውስጥ ተመልሶ የገባው። ወዲያውኑ ከአንድ ቁም ሳጥን ውስጥ የእጅ ጓንት አውጥቶ ካጠለቀ በኋላ ወደሌላው መደርደሪያ በማምራት አንድ የእንጨት መሠርሠሪያ የመሠለ የሕክምና መሳሪያ ይዞ ወደ ራስጌዬ መጣ። በዚያን ጊዜ ያ የተወጋሁት መድኃኒት ማደንዘዣ ኖሮ ሕሊናዬን ወደ መሳቱ ተቃርቤ ነበር።

ይሁን እንጂ ጭንቅላቴን በማወዛወዝ እንዳላስቸግራቸው ከጠረጴዛው ጋር አጣብቀው ከያዙኝ በኋላ በዚያ በመሰርሰሪያ የተላጠውን የራስ ቅሌን እንደሰበሩት ሁሉ ይታወሰኛል። እጅግ ያስጨነቀኝ ነገር ቢኖር ወላጆቼን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሳላያቸውና ሳልሰናበታቸው ብሞትስ የሚለው አሳብ ነበር። የኋላ ኋላ ግን የማደንዘዣው መድኃኒት እየተጫነኝ ሄዶ ከከባድ እንቅልፍ ላይ ወደቅሁ።

ከእንቅልፌ የነቃሁት ከብድ ቅዝዝ እንዳለኝ ነበር። ይብስ ብሎ ደግሞ የዚያ የመሠርሰሪያ ድምጽ አሁንም በጆሮ ግንዴ ላይ ማስተጋባቱን የገፋበት እየመሰለኝ እጮሃለሁ፤ አለቅሳለሁ። ጥቂትም ቢሆን አረፍ ያልኩት «አይዞሽ! ከእንግዲህ ምንም አትሆኝም!» ስትል ከጎኔ የነበረችው አስታማሚ ካጽናናችኝና ፊቴንም በማባበስ ካረጋጋችኝ በኋላ ነበር። እውነትም ዓይኔን ገለጥ ሳደርገው ያ እየጮኸ እረፍት የነሳኝ ድምጽ የመሰርሰሪያው ድምጽ ሳይሆን በኮርኒሱ ላይ

የተተከለው አየር ማቀዝቀዣ ኖሯል። ሌላ ያጨንኩት ነገር በግራና በቀኝ እርግብግቢቴ ላይ በትልልቅ ጉጠቶች የተጣበቀ ሽቦ መኖሩን ነው። ታዲያ እንደ እኔ ላለች ገና ዘልላ ላልጠገበችና ምኑንም ለማታውቅ ልጃገረድ ይህን መሰሉን መንፈሳዊና ሥጋዊ ሽክም መሸከሙ ከባድ ቢሆንም በእግዚአብሔር ርዳታ በመተማመን ቀጣዩን ቀናት እንደ ምንም እገፋቸው ጀመር። ሆኖም ግን ከሁሉም በላይ ያስቸገረኝ ነገር ቅዠት ነበር። በየጊዜው የሚሰጠኝ ማደንዘዣ ኃይል ተዳክሞ ከከባዱ እንቅልፍ ስነቃ የምሻገረው ወደ ቅዠት ነበር። ከሁሉም ግራ ያጋባኝ ደግሞ አዘውትሬ የምቃዠው ስለ አንድ ነገር መሆኑ ነው። ይኸውም የቀድሞው ትምህርት ቤት ጓደኛዬ ስለነበረው ስለ ጃስን ሌቨርተን ነበር በተደጋጋሚ የማልመው።

ከእርሱ ጋር ምን ጥፋት እንዳጠፋን ባላውቅም ግን ተከሰን ለፍርድ የምንቀርብ ይመስለኛል። በዳኛው ፊት እንድቆም የምደረገው ደግሞ እኔ ብቻ ስሆን ለዚያውም ልብሶቼን ሁሉ እንዳወልቅ በመገደድ መላ እርቃኔን ነው። ያም «ሐዋርያ» የሚመስለው ዳኛ ያለ ምንም ንግግር ዝም ብሎ ሲያየኝ ይቆይና በመጨረሻ ላይ ከወገቡ ጎራዴውን መዝዘ በማውጣት አንገቴን ይቀነጥሰዋል።

ታዲያ ከዚህ ቅዠት ምን ጊዜም የምነቃው ለብቻው የተቆረጠው ሞንቅላቴ ከምድር ላይ በሚወድቅበት ጊዜ ነው። ከዚያ በኋላ ግን ዳግመኛ ከኒን ተሰጥቶኝ እንቅልፍ እስከሚወስደኝ ድረስ ሌሊቱን ሙሉ የማሳልፈው ተንሰቅስቄ እንዳነባሁና የተጸነስኩበትን ዕለት እንደተራገምሁ ነው።

በዚህ መሰሉ ሁኔታ ስሠቃይ ከከረምኩ በኋላ ነበር አንድ ቀን ሌሊት ላይ ከጎኔ በሚያጓጉር የጣር ድምጽ የተቀሰቀስኩት። በዚያን ጊዜም የተኛሁት በሆዴ ተደፍቼ ሲሆን ዳሩ ግን ማን እንደዚያ እንዳስተኛኝ አላውቅም። መቼም በገዛ እጄ ተገላብጬ በዚያን መልኩ አንቀላፍቼአለሁ ማለት የማይታለምና የማይታሰብም ነው። እነኛ ከእርግብግቢቴ ላይ የተጣበቁት ሽቦዎች ግን አሁንም አልተላቀቁልኝም ነበር። ከዚያም በላይ ደግሞ አእምሮዬን አሰባስቤ ልብ ብዬ የተኛሁበት አልጋ ራስጌ የለሽ ሆኖ ቁልቁል ወደ ወለሉ የሚያሳየኝ ከመሆኑም በላይ በፕላስቲክ ድንኳን የተሸፈነ ተገለባባጭ ነበር። ወደ ወለሉም አሾልቄ ስመለከት ሁለት ነጫጭ የናይለን ጫማዎች በማየቴ አስታማሚዋ አጠገቤ ለመድረሷ በመተማመን

ሲስተር! ስል ተጣራሁ።

እርሷም «ምን ነው ፈለግሺኝ እንዴ?» አለችኝ ወደ እኔ ጎንበስ ብላ።

«ለመሆኑ የት ነው ያለሁት? ለምንስ. . . . ወደዚህ. . . . . አመጣችሁኝ» እያልኩ እንተባተብ ጀመር።

«እባክሽን ብዙ ለመናገር አትሞክሪ! አየሽ ገና በማገገም ላይ ስለሆንሽ ራስሽን ማድከም የለብሽም» አለችኝ በትሕትናና በማግባባት መንፈስ። እኔም ወዲያውኑ የተረዳሁት ነገር ቢኖር ይቺኛዋ አስታማሚ ቀደም ሲል ሙታንታዬን በመቀስ እንደተለተለችውና ፀጉሬን እንደላጨችኝ ዓይነት ግድየለሽና ጨካኝ ሴት አለመሆኗን ነው። እንደውም እጁን በፍቅር ትከሻዬ ላይ ጣል በማድረግ «አየሽ የቀዶ ጥገና ሕክምና ስላደረግሽ ሰላምና እረፍት ያስፈልግሻል። ስለዚህም ምንም መጨነቅና መጠበብ የለብሽም። እኔም በተቻለኝ መጠን ከአጠገብሽ ባለመለየት ባለኝ አቅም ሁሉ እረዳሻለሁ፤ ስለዚህ አይዞሽ የእኔ ቆንጆ! በርቺ!» ብላኝ ሄደች።

እውነትም ያች አስታማሚ ቃል እንደገባችልኝ በዚያን ሰሞን ከጎኔ ሆና ስለአበረታታችኝና ስለተንከባከበችኝ ነፍስ ወደ መዝራቱ ተቃርቤ ነበር። ከዚህም የተነሣ ነው ዙሪያ ገባውን ማጥናት የጀመርኩት። ያለሁበት ክፍል በማገገም ላይ ላሉ ታካሚዎች የተከለለ ሲሆን በውስጡም ስምንት አስታማሚዎችና ሕሙማኖች ነበርን። አስታማሚዎቹም በሁለት ሰዓት ውስጥ በመቀያየር አስፈላጊውን እርዳታ ያደርጉልን ነበር። በተለይም የእኔ አልጋ በፕላስቲክ የተከለለ በጀርባዬና በደረቴ ለመተኛት የሚያስችልና ፍሬም ያለው ሲሆን፥ አስታማሚዎቼ በየ 2 ሰዓቱ ቁልፉን ሲነኩት 180^0 ያዞረኛል። የተጠቀምኩበት ፍሬም ይወጣና በተቃራኒው እይታ እተኛለሁ። ይህም ገላዬ እንዳይላላጥና እንዳይቆስል ለመከላከል መሆኑን ተረድቼያለሁ።

ታዲያ ለተቀሩትም ሕሙማን ልክ እንደ እኔ ተመሳሳይ እንክብካቤ ቢደረግላቸውም አንዳንዶቹ ግን አስታማሚዎቹን መጨቅጨቅና ማመናጨቁን ይወዱ ነበር። በተለይም በአንድ ከጎኔ የተኛ በጭንቅ ላይ የነበረ አዛውንት ሊያጽናኑትም ሆነ እርዳታ ሊያደርጉለት የመጡትን ሁሉ እንደተሳደበና እንዳንቋሸሸ ነበር የሚውለው። በኋላም እንደተረዳሁት ያ ሰው ሚስቱንና ልጆቹን በሽጉጥ ገድሎ እራሱንም ለመጨረስ ቢሞክር እንዳልተሳካለትና ግንባሩ በመቦደሱ ለሕክምና እርዳታ እንደመጣ ነው። ሌላዋ ጨቅጫቃ ሕመምተኛ ደግሞ ጠና ያለች ሴት ስትሆን እርሷም ሌት ተቀን ሳትለይ አስታማሚዎቹን ሁሉ አንዴ ሲጋራ አምጡልኝ፥ አንዴ አይስክሪም ግዙልኝ እያለች ያሰለቸች ነበረች። ከዚህ በተረፈ ግን በክባድ የመኪና ግጭት ለአደጋ ተዳርጋ እንደ ነበረችው ጁዲና እንደ እኔው በውኃ ሳቢያ አንገቱ ተቆልሙሞ እንደነበረው ቶም ዓይነቶቹ ሕሙማን ጨዋዎች ነበሩ። ግን ምን ያደርጋል? ጁዲና ቶም ብዙም ሳይቆዩ ነበር ተከታትለው የሞቱት።

በተለይም ቶም ከአፍንጫው ላይ ተሰክቶለት የነበረው የኦክስጂን ጋንጋ በእንቅልፍ ልቡ ሲንፈራገጥ በመውደቁና በዚህም ሳቢያ በመሞቱ የሁላችንንም አንጀት ነበር የበላው።

ከዚህ የተነሣ እኔም ፍርሃት ወደቀብኝ። ምክንያቱም ምንነቱን የማላውቀው የህክምና መሳሪያ ከርግብግቢቴ ላይ ብቻ ሳይሆን በክንዴና በሆዴ ላይ ጭምር ተሰክቶ በማየቴ ነው። ያም ሆኖ ግን ተከታታዮቹ ቀናት በሰላም መሽተው መንጋታቸውን በማየቴ በመጠኑም ቢሆን መረጋጋቴ አልቀረም። ወደ ማገገሚያውም ክፍል ሌላ ሕመምተኛ የመጣው ጥቂት ቀናት ቆይቶ ነበር። ታዲያ ይህንንም ሰው ያስተኙት እንደ እኔው ባለ አልጋ ላይ ስለነበር የግድ በየሁለት ሰዓቱ መገላበጥ ነበረበት። እርሱ ግን አንዴም ቢሆን ሳይጨቃጨቅ በሰላም አይተኛላቸውም። ከዚህም የተነሣ ነበር አስታማሚዎቹ ዘወር በሚሉበት ጊዜ «አይዞህ እንደ እኔ ትለምደዋለህ! እያልኩ አበረታታው የነበረው፤ የሚያሳዝነው ግን እርሱም በመጣ በሁለተኛው ቀን ነበር ልክ እንደ ቶም አፍንጫው ላይ የተሰካለት ኦክስጂን ቱቦ ወድቆበት ሞቶ የተገኘው።

እውነቱን ለመናገር በሕይወቴ እንደዚያ ቀን አልቅሼ አላውቅም ለማለት እችላለሁ። ምክንያቱም ያ ሰው ሞትን እንደፈራው ያለታዛቢና አስታዋሽ በደረቅ ውድቅት ድፍት ብሎ በመገኘቱ ነው። ከዚያን ዕለት ጀምሮ ያ ክፍል ይብሱን እየቀፈፈኝና እየከበደኝ ሄደ። መቼም ማናችንም ብንሆን በጥቂት ቀናት ውስጥ ከጎናችን ሦስት አራት ሬሳ ሲጎተት እያየን አንፈራም ብንል የማይታመን ነው። እና እኔም ከዚህ የተነሣ ከዚያ ክፍል እንዲያስወጡኝ ከአስታማሚዎቹም ሆነ ከዶክተሮቹ ጋር መጨቃጨቁን ተያያዝኩት። እነርሱ ግን ምን ጊዜም የሚሰጡኝ መልስ ሁኔታዬ እስከሚለይ ድረስ ከዚያው መቆየት እንዳለብኝ ነው።

ግን ይሄ ሁኔታ . . . ሁኔታ . . . የሚሉት ነገር ምን ይሆን? ከአንገቴ እስከ እግሬ ድረስ መላወስ አለመቻሌን እንደሆነ አውቄዋለሁ፤ ተረድቼዋለሁ! ታዲያ ሐኪሞቹ ቆይ . . . . ታገሺ . . . . ጠብቂ . . . . የሚሉኝ ምን እስከሚመጣ ወይንስ ምን እስከሚፈጠር ነው? እንደ ጁዲና ቶማስ ሞቼ አርፌላቸው አስከሬኔን አውጥተው እስከሚጥሉት? ወይንስ ሌላ ተአምር ሊሠሩ?

ምዕራፍ ሁለት

ቀደም ሲል እንደገለጽኩት የቱንም ያህል ባማርርና ባለቅስም ከአናቴ እስከ መዋይቴ በሽቦ እንደተተበተብኩና በዚያ የፕላስቲክ አስር ቤት ውስጥ እንደታፈንኩ እንድቆይ ተደረገ። ቀናቱ በበረሩ ቁጥር ደግሞ ያ ያንጣብብኝ የነበረው የሞት ጥላ እየተገፈፈልኝ ለመሄዱ አሌ የማልለው ነው።

ይሁን እንጂ ወደዚያች የማገገሚያ ክፍል ከሚመጡት አብዛኞቹ እንደ እኔ በሕይወት የመቆየት ዕድል አልነበራቸውም። ምንአልባትም መሻሻል ታይቶባቸው ወደ መደበኛው የሕሙማን ክፍል አልፎ አልፎ ከሚወሰዱት ከአንዳንዶቹ በስተቀር የተቀሩት ዕጣ ፈንታ ግን በዚያው በተኙበት ለዘለዓለም ማሸለብ ነበር።

ታዲያ እኔ ድኜ ባልድንም ቅሉ ሞትን ግን ለጊዜውም ቢሆን ረስቼዋለሁ። ከዚያም ደጋግሞ ያስደነግጠኝ ከነበረው ቅዠት ለመላቀቅ ድከምከም እስከሚለኝና እንቅልፍ እስከሚቀረዝዘኝ ድረስ ስላለፈው ሕይወቴ ማብሰልሰልና በአሳብ መንጎዱን መፍትሔ ብዬ ተያይዤው ነበር። ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሳስታውስ አስተዳደጌ እንከን የለሽ እንደነበር የማይረሳኝ ነው። ወላጆቼም ከገቢያቸው ጋር የጨዋ ሕይወት በመምራታቸው በቤታችን ውስጥ ጥልና ጭቅጭቅ የሚባል ነገር ጨርሶም አይታወቅም ነበር። ጠዋት ተለያይተን ማታ እስከምንተያይ ድረስ እንነፋፈቃለን። ከዚያም ተቃቅፈን መሳሳም፥ መሳሳቅ፥ መፈንጠዝ ብቻ ነው። ለዚህ መሰሉ ሰላም ለሰፈነበትና ፍቅር ለነገሠበት ቤተሰብ ባለውለታ ደግም አባቴ ነበር።

የዚህ የአባቴ ስም ጆኒ ኤሬክሰን ይባላል። ማለትም የእኔ ስም በእንስታዊ ፆታ አጠራር ጃኒ ከመባሉ በስተቀር ስመ ሞክሼዎች ነን ማለት ነው። የተወለደው ደግሞ ልክ በ 1900 ዓ.ም እንደመሆኑም የሁለት ክፍለ ዘመናት ልጅ ነው ለማለት ይቻላል። ስለምን ፅንሱ በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ሆኖ ልደቱ ደግሞ በሃያኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ መሆኑ ነው። ከዚህም የተነሣ ይመስላል ተፈጥሮው ሁሉ በሁለት የተከፈለ ነበር። በአንድ በኩል ለአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን የሥነ ጥበብ እድገት ልዩ ፍቅር ሲኖረው በሌላ በኩል ደግሞ ለሃያኛው ክፍለ ዘመን የቴክኖሎጂ ምጥቀት በዚያው ደረጃ አክብሮትና አድናቆት ነበረው።

የሚገርመው እርሱ የተወለደው ግን ከአንድ በከሰል ችርቻሮ ንግድ ይተዳደር ከነበረ አልባሌ አባት መሆኑ ነው። ያም አንሶ የግድ አባቱን መርዳት ነበረበትና ከሰል በጋሪ በመጫን በየዕለቱ ከመንደር መንደር

እየገፋ ይሸጥ ነበር። በዚህም መሰሉ ፈታኝ ሕይወት ውስጥ ማለፉ ይመስለኛል የኋላ ኋላ ቁም ነገረኛ ቆራጥ ሰው ለመሆን የበቃው። ምን ጊዜም ቢሆን የእኔ አባት ለነገር የማይቸኩል መንፈሱ የተረጋጋና ደስታን የተላበሰ ሰው ነበር። በዚያ ላይ ደግሞ እንደ ሁኔታው የግሉን የሥራ መስክ በመክፈት ፍሬያማ ለመሆን በቅቶ ነበር። በጀልባ አከራይነት፥ በፈረስ ግልቢያ አሠልጣኝነት፥ በሠዓሊነት፥ በሕንጻ ገንቢነትና አናጺ ሙያዎች ላይ ሁሉ የተሰማራና ሰፊ ልምድን ያካበተ ነበር። እኔም በዚህ ሁለገብ ባለሙያነቱ በመደነቅ ነበር በአንድ ወቅት ይህን ሁሉ ችሎታ እንዴት ለማካበት ቻልክ? ስል ጠይቄው የነበረው።

እርሱም «ችግር ነው ያስተማረኝ ልጄ! አየሽ አንድ ሰው ዕድሉ እስካጋጠመው ድረስ ማናቸውንም እውቀት ከመቅሰም ወደ ኋላ ማለት የለበትም። ስለምን ያንን እውቀቱን አንድ ቀን የሚጠቀምበት ጊዜ ይመጣልና!» በማለት ነበር ምክር አዘል መልስ የሰጠኝ።

ታዲያ ፍልስፍናውንና የኑሮ ገጠመኞቹን ሳነጻጽራቸው አንዳንዶቹን ለማመን ይከብደኛል። ለምሳሌ አባቴ በ1932 (እ.ኤ.አ) በኦሎምፒክ ጨዋታዎች የትግል ውድድር ላይ ተሳትፎ የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት ሆኗል ብላችሁ እናንተስ መጠራጠራችሁ ይቀራል? ታዲያ ያንን የትግል ሙያውን ከከሰል ቸርቻሪነት ዘመኑ አንሥቶ ነበረ ያዳበረውና ደረጃ በደረጃ የገነባው፤ በመሆኑም ከአያሌ ድሎች ባሻገር ዓለም አቀፍ ዝናን ጭምር ለማትረፍ ችሎ ነበር።

በመንፈሳዊ ሕይወቱም ረገድ ቢሆን እንዲህ የዋዛ ሰው አልነበረም። በጎልማሳነት ዘመኑ ችግረኛ ሕፃናትን በግሉ ይረዳ ነበር። ከዚህም አልፎ አባል በነበረበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት በማቋቋም ለሕፃናቱ መጠለያ እስከማሰራት ያልተቋረጠ የምግብና የአልባሳት እርዳታ እስከ ማቅረብ ደርሶ ነበር። በዚህም መልካም ምግባሩ ሳቢያ ነበር ህብረተሰቡ «ሻምበል ጃኒ» በሚል የቅፅል ስም ይጠራው የነበረው። ከዚህ መሰል አድናቂዎቹ መካከል አንዱ የኋላ ኋላ ከእርሱ ጋር ለመጋባትና እኛንም ለማፍራት የበቃችው እናታችን ሊንዲ ነበረች። ሁለቱ ትዳር በመሠረቱበት ጊዜ የግላቸው የሆነ መጠለያ እንኳን የሌላቸው ምስኪኖች ነበሩ። ዳሩ ግን አባቴ የዋዛ ሰው አልነበረም፤ ከፈራረሰ መርከብ ላይ ያገኛቸውን የእንጨት ግንዲላዎችና ጣውላዎች በትከሻው ጭምር እየተሸከመ በማሰባሰብ የመጀመሪያዋን ጎጆውን ቀለሰ። ከዚያ በኋላ ትዕግሥትን በመላበስና በርትቶ በመሥራት ያችን ትንሿ ጎጆ አፍርሶ የዛሬውን የተንጣለለ ቪላችንን ለመሥራት ቻለ።

ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ሌላው የአባቴ መለያ ባህርይ ደግሞ እንደ ምንም በመፍጨርጨር የራሱን የሥራ መስክ የመክፈት ችሎታው ነው። በዚህም ጥንካሬውና መለኛነቱ ሳቢያ ቤተሰቡን ያለአንዳች ችግር ለመንከባከብ ችሎ ነበር።

ከዚህም የተነሣ ነው እኛ ልጆቹ ከሕፃንነታችን ጀምረን እንደ ፈረስ ግልቢያ፥ የውኃ ዋና፥ የቴኒስ ጨዋታና የመሳሰሉትን መዝናኛዎች የተለማመድነው። ለምሳሌ እኔ ገና በአራት ዓመት ጨቅላ እድሜዬ ብቻዬን ጫካና ሜዳውን በማቋረጥ ፈረስ ስጋልብ እውል ነበር። በተጨማሪም አባታችን በትርፍ ሰዓት የሚሠራቸውን አንዳንድ ነገሮች መኮረጁን ሙያ አድርገነው ነበር። በመሆኑም እንደየአቅማችን ሥዕሉንም፥ ቅርጻ ቅርጹንም፥ አናጢነቱንም መሞከራችን አልቀረም። በመደበኛው ትምህርታችን ረገድ ከጓደኞቻችን ልቀን እንድንገኝ የተቻለውን እርዳታ ያደርግልን ነበር።

ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ለደስታችን ምንጭ የነበረው የእናትና የአባቴ ፍቅር ነበር። አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ ተባብለው ከመተሳሰብና ከመተዛዘን ውጭ አንድም ቀን በመሀላቸው አምባጓሮ ተፈጥሮ አያውቅም። እኛን ልጆቻቸውን ከማቅረብ፥ ከማበረታታትና ከማሽሞንሞን በስተቀር አንድም ቀን ዘልፈውን ወይም ገሥጸውን አያውቁም።

ታዲያ ዛሬ የአልጋ ቁራኛ በሆንኩበት ጊዜ እንኳን አባቴ በቀን ሁለት ሦስቴ ተመላልሶ ሳይጠይቀኝ የዋለበት ዕለት የለም። ልክ እንደ ጥንቱ ሁሉ «በርቺ!» ማለቱን አልረሳውም፤ በዚያኑ መጠን ሊያዝናናኝና ሊያስቀኝ መሞከሩ አልቀረም። ሆኖም የቱንም ያህል ሊቀልደኝና ሊያጫውተኝ ይዋል እንጂ የመለያያችን ሰዓት ሲቃረብ ግን ዓይኖቹ እንባ ማቆራቸው አይቀሬ ነው። ዳሩ ምን ያድርግ! ከፍቅሩ የተነሣ ስሙን ሳይቀር ያወረሰኝ አባቴ አይደል! በገባ በወጣ ቁጥር እንደዚያ እንዳላሽበለበለኝና እንዳላሽሞነሞነኝ ሁሉ ዛሬ ራሴን ማዘዝ አቅቶኝ የአልጋ ቁራኛ ሁኜ ሲያየኝ ማዘን መተከዙ ይብዛበት እንዴ!!

በዚያ አንጻር እኔም ብሆን የአባቴ መሔጃ ሰዓት ሲደርስ መብሰክሰክና መዋለሌ አይቀርም። ያ ለደቂቃ እንኳን ቁጭ ማለት የማይወደው አባቴ ከእኔ ጋር ተጨብጦ መዋሉ አንሶት ሊለየኝ ሲል እንደዚያ መቆዘሙ አንጀት ነበር የሚበላው። «የእኔ አንሶ አባቴንም ለሥቃይ የዳረግከው ምን ብበድልህ ነው አምላኬ?» በማለት ዕለት በዕለት ወደ ፈጣሪያ እንዳማረርኩ ነበርኩ። እናቴ ግን እንደ አባቴ ቡቡና ሆደ ባሻ አልነበረችም። ከዚህም ጥንካሬዋ የተነሣ ነበር ከጎኔ ሌት ከቀን ባለመለየት ታስታምመኝ የነበረው። ምግቧንም ቢሆን ያቺ

ከሞት ያዳነችኝ እኅቴ ካቲ ጠዋት ማታ ከምታመላልስላት በስተቀር ከአጠገቤ ልውስ አትልም። የምትተኛውም ለሕመማን ጠያቂዎች ተብሎ ከተዘረጋ አንድ ሶፋ ላይ ነበር።

እንደዚሁም የታላቄ ታላቅ የሆነችው የሃያ ሦስት ዓመቷ እኅቴ ጀይ ባለ ትዳርና የአንድ ልጅ እናት ብትሆንም እርሷ ባመቻት ቁጥር እየተመላለሰች ትጠይቀኝ ነበር። ከሁሉም የማይረሳኝ ደግሞ በዚያ ራስጌ የለሽ አልጋ ላይ በደረቴ እንድተኛ በሚደረግበት ጊዜ እንኳ ዓይን ዓይኔን እያየች ለማዋራት እንዲመቻት በጀርባዋ የምትተኛው ነው። የሁላችንም ታላቅና እኔን በአሥር ዓመት የምትበልጠኝ ሊንዳም እንደዚሁም የሦስት ልጆች እናት ብትሆንም በመጣች ቁጥር ትንከባከበኛለች፥ ግን እንደ ካቲና ጀይ አይሆንልኝም።

ታዲያ ቀኑ በዚህ መልኩ ሳይታወቀኝ ያልፍና ወደ እንቅልፍ ዓለም የመሸጋገሪያዬ ድልድይ ግን ያለፉትን የሕይወት ገጠመኞቼን በአዕምሮዬ ማመላለስ ነበር።

በተለይም ደግሞ በዓይነ ሕሊናዬ ላይ ድቅን ይል የነበረው ያለፉትን ሦስት ዓመታት ያሳለፍኩበት የውድላው 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቴ ነው። ከግቢው ማማርና ውበት በተጨማሪም የእጅና የቅርጫት ኳስ፥ የቴንስና የሩጫ ሜዳዎቹ ለሚያዘወትራቸው ቀርቶ ለሚያያቸውም ማራኪ ነበሩ። እኔም ሁለገብ ስፖርተኛ ከመሆኔም ባሻገር የሴቶቹ የቴንስ ክበብ ፕሬዚዳንት ነበርኩኝ። እንዲሁም በትምህርት ቤቱ ውስጥ «ፍሬያማ ወጣቶች» በሚል ስያሜ ለተቋቋመው የተማሪዎች ማኅበር ገና በ15 ዓመቴ ፀሐፊ ሆኜ በመመረጥ ያሳለፍኳቸው ወርቃማ ዓመታት አይዘነጉም።

ከሁሉም ደግሞ ይህን ማኅበር በመወከል እኔና ሊቀመንበሩ ከርል ሄልሰን በአንድ ወቅት አኅራባቾችን ወደ ሆነው ወደ ቨርጂኒያ ግዛት ያደረግነው ጉዞ ምን ጊዜም የሚረሳኝ አይደለም። የተልዕኳችን ዓላማ አገር አቀፍ በሆነው በወጣት ክርስቲያኖች ጉባኤ ላይ ለመገኘት ነበር። ታዲያ የእግዚአብሔር ጸጋና በረከት ባልተለየው በዚህ ጉባኤ ላይ ንግግር እንዲያደርግ የተጋበዘው ባልደረባዬ ሄልሰን የሁሉንም ተሳታፊዎች ቀልብ የሳበ መልእክት ነበር ያስተላለፈው። በዚህ ንግግሩ ላይ ሄልሰን ያተኮረው በአሥርቱ ተእዛዛት ላይ ነበር። ነገር ግን ማናችንም ብንሆን ሕግጋቱን የማክበር ብቃት እንደሌለን በማስረጃ እያስደገፈና እያፍረጠረጠ ተናገረ። ያም ሆኖ ግን በንግግሩ መቋጫ ላይ ከኃጢአታችን ለማንፃትና ጽድቅን ለመውረስ የሚያስችል ግሩምና ድንቅ ዕድል እንዳለን አበክሮ አስገነዘበ። ይህም ጽድቅ በአንዱ

በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ብቻ መሆኑን በማስመር ነበር ንግግሩን የቋጨው።

እንደ እውነቱ ይህን መሰል መንፈስ ቀስቃሽ የሆነ ንግግር ስሰማ የመጀመሪያ ጊዜዬ ስለሆነ የሕሊና እረፍት ነስቶኝ ነበር። ከዚህም የተነሣ ነው በእንግድነት ካረፍኩበት መኝታ ክፍል በደረቅ ውድቅት በመውጣት በአቅራቢያዬ ካገኘሁት ዛፍ ሥር ደገፍ በማለት ሰማይ ሰማዩን እያየሁ በአሳብ የነጎድኩት።

ከዋክብት ብልጭ ድርግም እያሉ ብርሃናቸውን ሲረጩ ይታየኛል. . ይሁን እንጂ እኔ በዚያን ወቅት ለማየትም ሆነ ለመገናኘት የፈለግኩት ያንን የእግዚአብሔርን አንድያ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ ነበር።

ግን ኃጢአተኛ እስከሆንኩ እንዴት ወደ እርሱ መቅረብ . . . መጠጋት እችላለሁ? ከፊቱስ ለመቆም የሚያስችለውን ጽናት ከማን አገኘዋለሁ?

መቼም ገና የ17 ዓመት ኮረዳ ነኝና በዕድሜ ጨቅላ ነኝ ስል እራሴን በእራሴ ባጽናናም ኃጢአት መሥራቴን ግን አልከድም። በዚችው ዕድሜ ውስጥ እንደ አቅሜ ከሚመጥኑኝ ወንድ ልጆች ጋር ለመተዋወቅና ለመቀራረብ ችያለሁ። አንዳንዶቹንም በፍቅር ለማጥመድ ሞክሬያለሁ። በዚህ ሳቢያ ከመተቃቀፍና ከመተሻሸትም አልፎ ከንፈር ለከንፈር ተሳስመናል። ይብስ ብሎ አበድኩ ከነፍሱላችሁ በማለት ለችግርና ለጣር የዳረኳቸውም ጎልማሶች ስለመኖራቸውም የማይዘነጋኝ ነው። በእኔ የተነሣ የተደባደቡ፥ ገንዘባቸውንም የረጩ፥ ከትምህርታቸውም የተጓጎሉና ከወላጆቻቸው የተጋጩ . . . ሁሉ ነበሩ።

ያም ሆኖ ግን አንዴም ባለመስተጓጎል ነበር በየሳምንቱ እሁድ ከቤተ ክርስቲያን የማልለየው። ዳሩ ግን መንፈሴ እየተሸነፈ ስለሚያስቸግረኝ የማስበውና የማልመው ሁሉ ስለ ዓለማዊ ነገሮች እንጂ ስለ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባሮች አልነበረም። በመሆኑም እግሬ ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ወጣ ከማለቱ የምሮጠው አሁንም ጉብሎችና ኮረዶች ተሰባስበው ሙዚቃ ወደሚሰሙበት የጭፈራ አዳራሽ ወይም ሆታና ሁካታ ወደሚደምቅበት ኳስ ሜዳ እንጂ ምስኪኖችና ችግረኞች ወደሚረዱበት፥ ሕሙማን ወደሚጠየቁበት ወይም በእሥር ቀንበር የሚማቅቁ ወደሚገኙበት አቅጣጫ አልነበረም። ዛሬ ግን ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይግባውና ኃጢአተኛነቴን በማመን ለመጸጸት ችዬአለሁ። በዚያም ዛፍ ሥር ጋደም እንዳልኩ ለእኔ ሲል የሞተው ጌታ ኢየሱስ ደግሞ ደጋግሞ በዓይነ ሕሊናዬ እየታየኝ

ይቅርታ ጠይቄዋለሁ። ወደ መኝታ ክፍሌም ከመመለሴ በፊት ጌታ ራሱ በዮሐንስ 10፡10 ላይ ቃል እንደገባው የወደፊት ሕይወቴን የተባረከና የተቀደሰ እንደሚያደርግልኝ ተማምኜ ነበር።

ይሁን እንጂ ያ ጉባኤ ተጠናቅቆ ወደ ትምህርት ቤቴ ከተመለስኩ በኋላ ነበር ከመልከ መልካሙ ዲክ ጋር ለመተዋወቅ የቻልኩት ለዚህም አጋጣሚ የዲክ በትምህርት ቤታችን ውስጥ በተካሄደው የትግል ውድድር ማሸነፍ ነው። በውድድሩ ዕለት አባቴም ተገኝቶ ስለነበር የጥንት ትዝታው ተቀስቅሶ በስሜት እንደተናጠ ነበር ጨዋታው የተፈጸመው። በማብቂያውም ለዲክ ልዩ ፍቅር አድሮበት ኖሮ ወደ ቤታችን እንዲመጣ ጋበዘው። በዚሁ ሳቢያ ነበር እኔና ያ ቆንጆ ቁመተ ለግላጋና ደረተ ሰፊ ዲክ መቀራረብ ብቻ ሳይሆን ለጋብቻም እስከ መተሳሰብ የደረስነው። ከዚህም የተነሣ ከትምህርት ቤት ውጪ ያሉንን ትርፍ ሰዓታት ሁሉ የምናሳልፋቸው አብረን ነበር። ወላጆቻችንንም ቢሆኑ መፋቀራችንን በማወቅ እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ አብረን ብናመሽ እንኳን አይቆጡንም ነበር። ዲክ በእነርሱም ዘንድ በጥሩ ክርስቲያንነቱ ጭምር ልዩ አክብሮት አትርፎ ስለነበረ ያለ አሳብ ተያይዘን ከቤት እንወጣና እንገባ ነበር። ያም ሆኖ ግን እኔና ዲክ ግፋ ቢል ከመተቃቀፍና ከመሳሳም አልፎ ወደ ሌላ ብልግና አልተሸጋገርንም። በዚህ መልኩም ሁለት ዓመት እንደቆየን ወደ ኮሌጅ መግቢያ ፈተና ተቀብለን ሁለታችንም አኩሪ ውጤት በማምጣት አለፍን።

ታዲያ ዲፕሎማችንን በተቀበልንበት ዕለት ሁለታችንም ከፍተኛ ደስታ ይሰማን እንጂ ውስጥ ውስጡን ግን መባባታችን አልቀረም። ምክንያቱም ትምህርት ቤት እንደተዘጋ ዲክ ወላጆቹ በቅርቡ በሥራ ወደተዘዋወሩበት ሌላ ግዛት ስለሚሄድና በሚቀጥለውም ዓመት ከፍተኛ ትምህርታችንን የምንከታተልባቸው ኮሌጆች የተለያዩ በመሆናቸው ነው። እናም ያንን የምረታችንን ዕለት ሌሊት ያሳለፍኩት ወደ አምላኬ «ከእንግዲህ ከቤተሰቦቼም ሆነ ከፍቅረኛዬ ተለይቼ ምን ሊውጠኝ ነው? የተሟላና የተረጋጋ ሕይወት እንዳልመራሁ ሁሉ አሁን ለገለልተኛነት ልዳረግ ነውን? እባክህ የወደፊቱን ዕድሌን አንተ አቃናልኝ ጌታዬ!» እያልኩ በመማፀን ነው።

ይሁን እንጂ በዚህ ሆደ ቡቡነቴ እራሴን ሳልታዘበው አልቀረሁም። ለስሜትም ተገዢ የመሆኑ ጉዳይ ሳያሳስበኝ አልቀርም። ምክንያቱም የሕሊና ሰላም ነስተው ካጠቁኝ ሥጋቶች ውስጥ ዋናውና ተቀዳሚው ቅናት መሆኑ ነው። ይኸውም በመጪው የትምህርት ዘመን ከዲክ ጋር ስለምንለያይ እንደ አጋጣሚ ሌላ ፍቅረኛ ይዞ እኔን የረሳኝ እንደሆነስ ከሚል ፍርሃት የመነጨ ነበር። አዎን! እኛ ሰዎች ስንባል

በሕይወታችን ላይ ከደቂቃዎች በኋላ እንኳን ምን እንደሚደርስ ባናውቅም፤ ግን ስለ ወደፊቱ ሕይወታችን አርቀን በማሰብ መጨነቅና መጠበባችን አይቀሬ ነው። የሁላችንም የአዳም ዘሮች ድክመት ይህ ነውና እኔም ከቀናት በኋላ ከባህር ውስጥ ዘልዬ በመግባት ለዚያን መሰሉ አደጋ እንደምጋለጥ ባለማወቅ ጭንቀቴ ሁሉ ከዲክ ጋር ስለማሳልፋቸው የወደፊት የፍቅር ዓመታትና ስለምንመሠርተው ትዳር ነበር!

ምዕራፍ ሦስት

ዲክ ትምህርት ቤታችን እንደተዘጋ ወደ ሌላ ግዛት ሄዶ ስለነበር የአልጋ ቁራኛ ሁኜ የመቅረቴን ዜና የሰማው ውሎ አድሮ ነበር። እርሱም ከራስጌዬ ተቀምጦ ለሚወረውራቸው አንዳንድ የማጽናኛ ቃላት ጆሮዬን ሙሉ ለሙሉ ባልሰጣቸውም ዳሩ ግን «ከልባችን በእግዚአብሔር ካመንን ማናቸውንም የሚደርስብንን ችግርና ፈተና ለበጎ እንደሚያደርጋቸው ቃል ገብቶልናል» ሲል ተናግሮ ነበር።

እኔም ከአፉ ላይ ቀለብ በማድረግና ንዴት በተቀላቀለበት መንፈስ «ለምን እንዲህ ትላለህ ዲክ? ይኸው እኔ እዚህ አልጋ ላይ ከተጣበቅሁ ከወር በላይ ሆነኝ፥ እግዚአብሔር ያደረገልኝ ምንም እርዳታ የለም ስል መለስኩለት። ምሬቴንም በመቀጠል አየህ ሌላው ቀርቶ አደንዛዥ ክኒኖች ካልወሰድኩ እንቅልፍ የሚባል ነገር በዓይኔ ላይ አይዞርም። በዚያ ላይ ደግሞ በቅዥት ዓለም እንደዋኘሁ ነገር ዓለም ተዘበራርቆብኝ እንደቀባጠርሁ አነጋለሁ። ይህም አንሶ ደግሞ የደረቀ ሬሳ ይመስል አንዱ በጀርባዬ ከተንጋለልሁ ንቅንቅ ሳልል ነው የማድረው። ታዲያ እንግዲህ እግዚአብሔር ማናቸውንም ነገር የሚያደርስብን ለበጎ ነው ያልከው ከምኑ ላይ ነው?» ስል የሆዴን ብሶት ገለጽኩለት።

እርሱ ግን ትዕግሥት በተላበሰና ረጋ ባለ አንደበት «አይዞሽ ጃኒ!» ሲል ወደ ጆሮዬ ጠጋ ካለ በኋላ፥ «የቱንም ያህል ችግርና ሥቃይ ቢደርስብንም በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ማመን አለብን። ይህን እስካደረግን መልካም ዕድል እንደሚገጥመን አትጠራጠሪ» ብሎ መጽሐፍ ቅዱሱን ገለጥ አደረገ።

እኔ ግን በመሽቀዳደም «ምንም ነገር እንድታነብልኝ አልፈልግም!» ስል ጮህኩ። በዚህ ንግግሬ ዲክ እጅግ ከማዘንም አልፎ እንባውን እያፈሰሰ ከአልጋዬ ሥር ከተንበረከከ በኋላ «አይዞሽ ጃኒ! እግዚአብሔር አንዱን ቀን ጎብኝቶ እፎይታን እንደሚያላብስሽና ደስታን እንደሚያቀዳጅሽ አመኜ» ብሎ ይጸልይልኝ ጀመር። በዚህ መልኩ ብዙ ደቂቃዎች ካሳለፈ በኋላ ነበር ከተንበረከከበት በመነሣት «በቅርብ ተመልሼ መጥቼ እስከምጠይቅሽ ድረስ እግዚአብሔር ምሕረቱን ይላክልሽ» ብሎኝ በመሰናበት የወጣው።

ልክ የድሮው ፍቅሬ የታደሰ ይመስል በዚያን ዕለትም ሆነ በተከታታይ ቀናት ሁሉ ስለ ዲክ ሳላስብ ውዬ አላውቅም። እንባውን እያዥጎደጎደ የጸለየልኝ ጸሎትና የለገሰኝ ምክር ሁሉ አልተረሳኝም። እንዲያውም እርሱ ገና ወጣ ከማለቱ በውስጤ የመረጋጋት መንፈስ

ሰፍኖ ኖሮ የፊቴን መለዋወጥ ያጤነችው አስታማሚዋ አኒታ እንኳን «እንዴት ነው ዛሬ ጃኒ? ቅልል ያለሽ ትመስያለሽ!» ስትል ተናግራኝ እንደነበር አልረሳም።

እኔም «አዎን ዛሬ የጨፈገገኝ ሁሉ ለቆኛል» ስል ነበር የመለስኩላት።

እርሷም «አደራሽን ይህ የዛሬው ሁኔታሽ እንዳይለወጥ» በማለት ነበር የተለየችኝ።

ይሁን እንጂ በዚያኑ ዕለት ማታ ላይ ሊጠይቀኝ የመጣው ሌላው የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ጀሰን በመጠኑም ቢሆን ያንን የተረጋጋውን መንፈሴን ሊያናጋው ሞክሮ ነበር። በጨዋታ ጨዋታ የዲክን ነገር አንሥተን ስለነበር ቀን ላይ መጥቶ እንደ ጠየቀኝና ሲጸልይልኝም ውሎ መሄዱን ለጀሰን ነገርኩት።

ሆኖም ጀሰን የጸሎትን ጠቀሜታ በማናናቅ «እግዚአብሔር ይረዳኛል ወይም በሆነ ተአምር እድናለሁ ብለሽ አጉል ከምትጽናኚ ይልቅ በርትተሽ ሕክምናውን መከታተል፥ እንዲያውም ወላጆችሽ ወደ ተሻለ ሆስፒታል እንዲያዘዋውሩሽ መጠየቅ ይሻልሻል» በማለት ነበር የታደሰውን ተስፋዬን ሊያጨልመው የሞከረው። እኔ ግን ዲክ የለገሰኝን ምክር ባለመርሳት ማናቸውም ነገር ቢሆን እግዚአብሔር ያለ ምክንያት አያደርገውም። ስለዚህም በእኔ ላይ ያደረሰው አደጋ ለበጎ ዓላማ መሆኑን አንድ ቀን እንደምመሰክረው አልጠራጠርም በማለት በተራዬ ተስፋ በማስቆረጥ ሸኘሁት።

በማግስቱ ልዩ ምርመራ ሊደረግልኝ ወደ ሌላ ክፍል ተወስጄ ነበር። ሐኪሞቹም በሆዴ በማስተኛት በጀርባዬ ላይ ጥናታቸውን ሲያካሂዱ ቆዩ። ምንም እንኳን በየመሀሉ ጣልቃ በማስገባት የሚወረውሯቸው አንዳንድ የሕክምና ቃላት ባይገቡኝም፥ ከቀድሞ ሁኔታዬ የተሻሻለ ነገር ላለመኖሩ ተረድቼ ነበር። ከዚህም የተነሣ እነርሱም መጨነቃቸውን አውቄዋለሁ። ታዲያ በመጨረሻ ላይ ነበር በአከርካሪ አጥንቴ ውስጥ ካለው ፈሳሽ በረጅም መርፌ መጥጠው በመቅዳት ወደ ቤተ ሙከራ ተወስዶ ልዩ ምርመራ እንዲካሄድበት ያዘዙት። ከዚያም በጀርባዬ ገልብጠው በማስተኛት የተቀረውን የሰውነት ክፍሌን በጀሮ ማዳመጫ መሣሪያቸው ሲያስሱት ቆዩ። በመቀጠልም በዚያው በተኛሁበት ሁኔታ ፎቶግራፍ እንድነሣ ካደረጉ በኋላ ወደ ማገገሚያ ክፍል እንድመለስ አደረጉ።

ይሁን እንጂ በዚያኑ ዕለት ምሽት ተረኛ የነበረውን ዶክተር ሼሪልን ለምን ቁርጤን ፍርጥርጥ አድርጋችሁ አትነግሩኝም

አልፈራም? ስል በጥያቄ ወጥሬ ይዤው ነበር። እርሱም ከመጨነቁ ብዛት የተነሣ ነበር። «ለሞት የሚያሰጋ ነገር ባይኖርም የደረሰብሽ አደጋ እጅግ ከባድ በመሆኑ ከአንገትሽ በታች በሆነው የሰውነትሽ ክፍል ላይ በቀላሉ ሊወገድ የማይችል ችግር አስከትሏል የሚል ነው ጥርጣሪያችን» በማለት መልስ ሰጠኝ።

እኔም ከአፉ ቀበል በማድረግ «እሪ ለካስ ትሞታለች ስትሉም ሰግታችሁ ኖሯል?» ስል በተራዬ በማሾፍ ጠየቅኩት።

«ለምን አንሰጋም ጃኒ? ለመሆኑ እዚህ ክፍል ውስጥ ከጎንሽ ተኝተው ከነበሩት ሕሙማን እንኳን ስንቶቹ ናቸው በሞት የተለዩት?» በማለት ጥያቄዬን በጥያቄ መለሰልኝ።

«እንግዲያውማ እኔ እስከ ዛሬ በሕይወት በመቆየቴ ዕድለኛ ነኝ ልበላ!» አልኩት አሁንም የፌዝ ፈገግታ እያሳየሁ።

«ምን ዕድለኛ ብቻ! መንፈሰ ጠንካራና ብርቱ ልጅም ነሽ እንጂ! አለበለዚያማ እንደ ሌሎቹ ደካማ ብትሆኚ ኖሮ ገና ዱሮ ተሰናብተሽ ነበር። በመሆኑም እድሜሽን ያራዘምሽው በገዛ ጥረትሽና ብርታትሽ ብሎም በግል መንፈሳዊ ጽናትሽ እንጂ በእኛ እርዳታ አለመሆኑን ልታውቂው ይገባል።» «ስለቸርከኝ የምስጋና ቃላት አመሰግናለሁ። ያም ሆኖ ግን እዚህ የምታደርጉልኝ እርዳታ ከሌለ ለምን ወደ ቤቴ እንድመለስ አትፈቅዱልኝም?» ስል ሌላ ጥያቄ አቀረብኩለት።

«ገና ምኑን ተያያዝነውና ነው ወደ ቤትሽ የምትመለሺው ጃኒ? አየሽ የእኛ ዕቅድ ዛሬ ከአከርካሪው አጥንትሽ የተቀዳው ፈሳሽ ውጤት እንደታወቀ ብድጋሚ ኦፕራሲዮን ልናደርግሽ ነው። ስለዚህ ልትታገሺና የሚመጣውን ሁሉ በቆራጥነት ልትጋፈጪው ይገባል» አለኝ ለማበረታታ ሳቅ እያለ።

እኔም ነገር መጎተቴን አሁንም ገፍቼበት «በድጋሚ ኦፕራሲዮን መሆኔ ለምን አስፈለገ?» ስል ጭንቀት እየገባኝ ጠየቅኩት። «ያስፈለገውም በወደቅሽበት ወቅት ተለያይተው የነበሩትን አራተኛውንና አምስተኛውን የደንደስ አጥንቶችሽን ለማያያዝ ነው። ከዚያ በኋላ ነው ከአንገትሽ በታች ያለውን የሰውነት ክፍልሽን ለማንቀሳቀስ መቻል አለመቻልሽን የምናውቀው።» ይህን እንደሰማሁ ቁርጤን አውቄ ልረፍ ስል «ለመሆኑ መቼ ነው ኦፕራሲዮን ልታደርጉኝ ያቀዳችሁት?» በማለት የመጨረሻውን ጥያቄዬን ሰነዘርኩ።

«ነገ!»

ድንግጥ እንደማለት ብዬ «ነገ?» ስል ጮህኩና ወዲያውኑም እራሴን በማረጋጋት «ጥያቄዎቼን በትዕግሥት አዳምጠህ ስለመለስክልኝ አመሰግናለሁ» የሚሉትን ቃላት ወርውሬ ዓይኖቼን ከደን አደረኳቸው።

ያንን ሌሊት ያሳለፍኩት ዲክ የተናገራቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት መላልሼ በአእምሮዬ በማብላላት ነበር። አዎን! እግዚአብሔር እራሱ ማናቸውንም ነገር ያለ ምንም ምክንያት እንደማያደርግ ቃል ገብቶልኛል። ስለዚህ እኔንም ለዚህ መሰሉ አደጋ ያጋለጠኝ አንድ ያዘጋጀልኝ ዕድል ፈንታ ቢኖር ነው። ደግሞስ በሮሜ 8፡28 ላይ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ በመመራት «እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን» ሲል ጽፎልን የለም! ከእንግዲህ የፈለገው ነገር ቢደርስ በከንቱ ላልደነግጥና ላልብረከረክ፣ ተስፋም ላልቆርጥ ወሰኜ ነበር ያሸለብኩት።

የዶክተር ሼሪል አባባል ለየት ያለ ቢሆንም የእኔ እምነት ግን የአከርካሪ አጥንቴ ኦፕራሲዮን መሆኑና የደንደስ አጥንቶቼ መገጣጠም ወዲያውኑ የተሟላ ጤንነት እንደሚያወርሰኝ ነበር። ማለትም በየደቂቃውና በየሰዓቱ በአእምሮዬ ሳመላልስ የነበረው ተስፋና ምኞት በእነኛ እጆቼ ዳግመኛ እንደምበላባቸውና በእግሮቼም ወዲያና ወዲህ ብዬ እንደምዘዋወርባቸው ነበር።

ከኦፕራሲዮኑም ከፍል እንደወጣሁ የተወሰድኩት ወደ ቀድሞው የማገገሚያ ክፍል ሳይሆን ለብቻዬ ወደተዘጋጀልኝ መኝታ ቤት በመሆኑ ይህም በራሱ ለየት ያለ እምነት አሳድሮብኝ ነበር። በማግስቱም ከእናትና ከአባቴ ጋር ሞቅ ያለ ጨዋታ ይዘን በምንነጋገርበት ጊዜ ነበር ዶክተር ሼሪል በሩን አንኳኩቶ የገባው። በዚህም ባልተጠበቀ ጉብኝቱ ሁላችንም ብንሆን በየግላችን ፈገግታ ለግሰነዋል። ሰላምታም ከተለዋወጥን በኋላ ነበር እንደ አጋጣሚ እናቴ «ታዲያስ ኦፕራሲዮኑ እንዳሰባችሁት ተሳካላችሁ?» በማለት ነገር የጫረችው። እርሱም ሳቅ አለና «በመሳካቱማ ነው እመቤቴ ልጃችሁን ከብባችሁ ለመጫወት የቻላችሁት» ሲል መለሰላት።

እናቴ ላቀረበችው ጥያቄ ተገቢውን መልስ ባለማግኘታና ባለመርካቷ ነው መሰለኝ ፊቷ ከስክስ እንደማለት ብሎ «እዚህስ ላይ እውነትዎን ነው!» የሚሉትን ቃላት ብቻ ተናግራ ዝም አለች።

ይሁን እንጂ የዶክተር ሼሪል አመጣጥ ለካስ ለእኔና ለወላጆቼ ጭምር ለየት ያለ ማብራሪያ ለመስጠት ኖሮ ጉሮሮውን በመጠራረግ ትኩረታችንን ከሳበ በኋላ ፈገግ ለማለት እየሞከረ «ሁላችሁም ብትሆኑ ከልብ እንድታጤኑልኝ የምሻው ነገር አለ። ይኸውም ጄኒ ከሕመሟ ሙሉ በሙሉ ለመዳን ረዘም ያለ ጊዜና ብዙ ትዕግሥት የሚጠይቅ

መሆኑን ነው። ከዚህም የተነሣ ምናልባት መጪዎቹ ቀናትና ወራት የትፍስህትና የደስታ ላይሆኑልሽ ይችሉ ይሆናል። ምክንያቱም ጃኒ በአልጋ ላይ የምታሳልፈው ጊዜ ረጅም እንደሚሆን ስለደረስንበት ስለምትከፍሉት መሥዋዕትነትና ስለሚገጥማችሁ ውጣ ውረድ ከአሁኑ እራሳችሁን ልታዘጋጁት ይገባል። ይህ ደግሞ ከምንም ነገር ይበልጥ የሚጠይቀው የእያንዳንዳችሁን የመንፈስ መረጋጋት ነው። ምናልባትም ጃኒ ከሐኪም ቤት የመውጣት ዕድል ከማግኘቷ በፊት ጓደኞቿ የኮሌጅ ትምህርታቸውን ሊጀምሩና ሊገፉበትም ይችሉ ይሆናል። እንደዚሁም አንዳንዶቹ ትዳር ሊይዙና ቤተሰብ እስከመመሥረት ይደርሱ ይሆናል። ስለዚህ አሁንም አበክሬ የማስገነዝባችሁና የምመክራችሁ ፈታኝ የሆነውን መጪውን ጊዜ በትዕግሥትና በቆራጥነት ልትቋቋሙት እንደሚገባ ነው» ሲል በረጅሙ ተንፍሶ ንግግሩን አቆመ።

በዚያን ጊዜ በሁለቱም ወላጆቼ ፊት ላይ ድንጋጤ ባይም የሞት ሞቴን ፈገግ እንደማለት ብዬ «ይህማ የታወቀ ነው ዶክተር! ምክንያቱም ማንም ሕመምተኛ ቢሆን በሚደረግለት የሕክምና እርዳታ እየታገዘ በተስፋ መጠበቅ አለበት እንጂ ለምን ዛሬውኑ አልዳንኩም ወይም ሙሉ ጤነኛ አልሆንኩም ለምንስ እንደ ጓደኞቼ አልሮጥኩም አልዘለልኩም ማለት አይኖርበትም» ስል የተጨነቁትን ወላጆቼን ዘና ላደርጋቸው ሞከርኩ።

ዳሩ ግን እናቴ በእኔም መልስ አሰጣጥ ባለመርካት የዶክተሩን ዓይኖች አተኩራ እያየች «ይቅርታ አድርግልኝና ዶክተር፥ ከአነጋገርህ እንደተረዳሁት ጃኒ በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ወደ ኮሌጅ በመግባት ትምህርቷን መከታተል እንደማትችል ነው። እኛ ደግሞ ይህን መሰሉ ያልታሰበ ችግር ይደርሳል ብለን ባለመጠርጠር ለትምህርት ቤቱ የሚከፈለውን ማንኛውንም የዓመት ሂሳብ ቀደም በማለት ነበረ የሸፈንነው፤ ታዲያ አሁን እንዳልከው መጪው የትምህርት ዘመን የሚያመልጣት ከሆነ የከፈልነውን ገንዘብ ከአሁኑ እንዲመለስልን መጠየቁ የሚሻል አይመስልህም?» ስትል በዘዴ የተሸፋፈነ ጥያቄ አቀረበችለት። እርሱ ግን በነገር አካሄዱ በመንቃት «ይሻል ይመስለኛል» የምትለውን መልስ ብቻ ሰጣት።

«አሃ! አሁንማ ሁሉ ነገር ግልፅ ሆኖልኛል። እንደ እናንተ እምነት ጃኒ ቢያንስ ለአንድ ዓመት የአልጋ ቁራኛ ሆና ትቆያለች ማለት ነው» አለችና እናቴ መልስም ባለመጠበቅ አንገቷን ዘንበል አድርጋ አቀረቀረች። በዚያን ጊዜ ነበር ዶክተር ሼሪል ወደ እናቴ ቀርቦ እጁን በትከሻዋ ላይ ጣል ካደረገ በኋላ «አዩት እመቤት ኢሬከሰን፥ እኛ ሰዎች ስንባል መጀመሪያውኑ መፈጠራችን ለሞት መሆኑን ማወቅ አለብን፤ ከዚያም በላይ ደግሞ ከተፈጠርንበት ዕለት አንሥቶ አንዳንድ

ያልታሰቡ ችግሮች ሊያጋጥሙን እንደሚችሉ ነው። በዓለማችን ላይ በየጊዜው ሲከሰት እንደምናየው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶች በጦርነት፥ በመኪና ግጭትና በተለያዩ ሕመሞች ይቀጫሉ። እናም ከዚህ በመነሣት ይህን በጃኒ ላይ የደረሰውን አደጋ እንደተለየ ነገር አድርገን ማየት የለብንም። በዕድሜአችን ውሱንነትና የእኛን ደካማነት በማጤን እውነታውን ለመጋፈጥ ደፋርና ጠንካራ መሆን ይጠበቅብናል። እናም የመንፈሳዊ ጽናትን አስፈላጊነት በማስመልከት ይህን ከተናገርኩ ዘንዳ የጃኒን የወደፊት ሕይወት በማስመልከት ደግሞ ቁርጡን ላሳውቃችሁ ስለሆነ ይህን ለመስማት ፈቃደኛ መሆን አለመሆናችሁን በቅድሚያ ብትገልጹልኝ?» ሲል በለሰለሰ አንደበት ጥያቄ አቀረበ። አሁን ደግሞ በድንጋጤ ከተቀመጠበት ቱር ብሎ የተነሣው አባቴ ነበር። እርሱም በተጎለጎሉ ዓይኖቹ ወደ ዶክተሩ እያየ «በል እንጂ! ቁርጡን ንገረንና እንረፈው» ሲል ሲቃ እየተናነቀው ተናገረ።

«ጥሩ» እንግዲህ የጃኒን የወደፊት ዕድል በማስመልከት በሕክምና ባለሞያነታችን ያረጋገጥነው ነገር ቢኖር ሁለቱም እግሮቿ ሽባ ሆነው መቅረታቸውን ነው። በመሆኑም በሰው ሽክም ወይም በሚገፉ ጋሪ ወይም በተሽከርካሪ ከመንቀሳቀስ በስተቀር በራሷ ኃይል አንዲትም ስንዝር ያህል መላወስ አትችልም» ብሎ ትንፋሹን ዋጥ አደረገ።

«እጆቼስ? እጆቼስ? እነርሱም በድን ሆነው ቀርተዋል ማለት ነው?» ስል ነበር በተራዬ የጮኽኩት።

«የእጆችስ ጉዳይ እንኳን ገና አልለየለትም። የእኛ ግምት ግን አንድ ቀን ልታንቀሳቅሺያቸው እንደምትችዪ ነው። ያም ሆኖ ግን ግፋ ቢል ምግብ ቆርሰሽ ለመብላት ወይም ብዕር ይዘሽ ለመጻፍ ከሚያገለግሉሽ በስተቀር ከባድ ሥራ ለመሥራት አያስችሉሽ ይሆናል። ያም ሆነ ይህ ከአንድ አልባት እስከምንደርስ የግድ ልትታገሺን ይገባል።»

ይህን ጊዜ እናቴ «ወይ ልጄን! ጉድ ሆንኩ ልጄን!» እያለች ታለቅስና ትንሰቀሰቅ ጀመር። እኔም እንደ አቅሚቲ ላጽናናት በመሞከር «አይዞሽ እማማ! ዶክተር ሼሪል እንዳለው ሽባ ሆኜ ላልቀር እችል ይሆናል። ምክንያቱም እዚህ ሆስፒታል ውስጥ በእኔ ዓይነቱ ሕመም ተለክፈው ብዙ የዳኑ መኖራቸውን በመስማቴና እኔም አንድ ሁለቱን በማየቴ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ እኔም አንድ ቀን የማልድንበትና እንደ ቢጤዎቼም እጅ እግሬን የማላዝበት ምክንያት የለም» በማለት ፈገግ አልኩ።

ታዲያ እንደዚያ በማለት አጽናንቼያቸው ሌላ ሌላ ጨዋታ እያነሣሁ አእምሮአቸውን ለማደስ ብሞክርም ቀኑ መሽቶ እስከሚለዩኝ ድረስ ጎዘኑ ሙሉ ለሙሉ አልለቀቃቸውም ነበር። ደግሞም ለእናቴ ድርብርብ ጭንቀት የሆነባት እንደ በፊቱ የማገገሚያ ክፍል ቆይታችን ሁሉ በዚህን ክፍል ውስጥ ለመኝታ የሚያመች ነገር ባለመኖሩ ብቻዬን በመተው ልትለየኝ በመገደዱ ነው። በበኩሌም ቢሆን ያንን ሌሊት ያሳለፍኩት እንደ ልማዴ አንዴ በማልቀስ፥ ጋብ ሲልልኝ ደግሞ ወደ አምላኬ በመጸለይ ነበር።

መቼም እንደ ሰው ልጅ ጽኑና ብርቱ ፍጡር የለምና እኔም ውሎ እያደረ የደረሰብኝን ችግር እየተላመድኩትና እራሴንም እያበረታታሁ ሄድኩ። ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን አንዳንዴ ላልታሰበ ብስጭትና ጎዘን መዳረጌ አልቀረም። ለምሳሌ በአንድ ወቅት ሁለት የትምህርት ቤት ጓደኞቼ ሊጠይቁኝ መጥተው ስንጨዋወት በመሀሉ የተፈጠረው ነገር አይረሳኝም። ነገሩን የጫረችው ጃኪ የምትባለዋ የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ስትሆን፥ እርሷም እንደ ዋዛ ነበር «ለመሆኑ እዚህ ቤት መስታወት አለ ወይ?» ስትል የጠየቀችው።

«እኔም «ኧረ የለም!» ስል ከብደት ባለመስጠት መለስኩላት።

«ታዲያ ፊትሽን አይተሽው አታውቂም ማለት ነዋ?» አለችኝ አሁንም እንደ ቀልድ።

«አዎን! አይቼው አላውቅም» አልኳት ምንም ባለመጠራጠር ፈገግ ብዬ።

«ምን ያህል መሰለሽ የተለዋወጥሽው ጃኒ» ስትል አሁንም ደግሞ በመቆርቆር ስሜት ተናገረች።

እኔ ግን እራሴን ግድ የለሽ ለማስመሰል ያህል «ከአሁን ወዲያ የእኔ ፊት ታየ አልታየ ምን ሊያመጣ ብለሽ ነው?» ስል ነገሩን በማናናቅ ለማረሳሳት ሞከርኩ። ታዲያ ነገሩን በዚያን መልኩ አለባብሼ ልለፈው እንጂ ቀኑን ሙሉ ሆድ ሆዴን ሲበላኝ በመዋሉ የማታ ማታ እጎቴ ካቲ መጥታ እግሯ ገና ከመኝታ ክፍሉ ገባ ከማለቱ ነበር መስታወት አምጥተሽ ፊቴን ካላሳየሽኝ በማለት ውጥር አድርጌ የያዝኳት። እርሷም ነገሩ ገብቷት በአካባቢው መስታወት የለም ስትል ሰበብ አስባብ ለመፍጠር ሞከረች። ዳሩ ግን ጭቅጭቄ ፋታ ስለነሳት ከገባችበት ገብታ መስታወት በመፈለግ ከፊት ለፊቴ ይዛው ቆመች።

«በእውነቱ እንደዚያ ቀን መፈጠሬን የረገምኩበት ዕለት የለም! በዚያች ቀድሞ በማውቃትና አይቼ በማልጠግባት ፊተ ክቧና ፍልቅልቅ ጃኒ ምትክ የምትታየኝ የነበዘች፥ የበለዘች፥ የተኮላመነችና

የገረጣች ጀኒ ናት። እነኛ ከብላላዎቹ ዓይኖቼ ጎድጉደው ሟሽሸዋል። ያም ትከሻዬ ላይ ወርዶ ይዘናፈል የነበረው ሐር ፀጉሬ አሁን ከወጎኒ ቤት እንደ ገባ እስረኛ ተቀምቅሟል! በአጭሩ ከሌላ ዓለም የመጣች ልዩ ፍጡር እመስል ነበር።»

ምድር ሰማዩ እንደ ዞረብኝ ተስፋ እንደ ቆረጥሁና ሆድ እንደ ባሰኝ የተረዳችው እጎቴ መስታወቱን ከፊቴ ላይ ዘወር በማድረግ ከወረወረችው በኋላ ከአንገቴ ላይ ተጠምጥማ አለቀሰች። እኔም አብሬያት ተንሰቀሰቅሁ። ለብዙ ደቂቃዎች ያህልም በዚያ ሁኔታ ከቆየን በኋላ ቁጭቴ በረድ ብሎ መንፈሴ በመረጋጋቱ ለየት ስላለ ነገር ማብሰልሰሉን ተያያዝኩት። ብዙ ካወጣሁና ካወረድሁ በኋላ ከአንድ ውሳኔ ላይ በመድረሴ «ለምን ከዚህ ሁሉ ጭንቅ እንድገላገል አትረጂኝም ካቲ!» ስል አስተዛዝኜ በጆሮዋ ሹክ አልኩኝ።

እርሷም ያቀፈችውን አንገቴን ለቅቃ ቀና ካለች በኋላ ፈገግ እያለች «እስቲ በምን መንገድ ልረዳሽ እንደምችል ንገሪኝና ልወቀዋ» አለችኝ።

«የምትረጂኝ ከዚያ የእንቅልፍ ክኒን ጨማምረሽ በመስጠት ይሆናል» አልኩና ብልቃጡ ወደሚቀመጥበት አቅጣጫ በዓይኔ ጠቀስ አደረግኳት።

እርሷ ግን እንደ መገረምና እንደ መደንገጥም ብላ ከአልጋው ላይ ብድግ ካለች በኋላ «ለምን?» ስትል ጠየቀችኝ።

«ሞቼ እንድገላገል ነዋ!» ስል ግልጹን ነገርኳት።

«እና እኔው ሆንኩ ሙቺ ብዬ ኪኒን የምሰጥሽ!» ብላ በምሬት በመናገር ፊቷን ካዞረች በኋላ ተንሰቅስቃ ታለቅስ ጀመር።

«እባክሽ አታልቅሺ ካቲ፥ ሞትን የመረጥኩት እኮ እናንተን ከማሠቃይ ብዬ ነው» አልኩ እኔንም ሣግ እየተናነቀኝ።

«ምኑ ላይ ነው ሥቃዩ? አንቺ በሕይወት ኑሪልን እንጂ ለምን ለዘላለም ባሪያዎችሽ ሆነን አንቀርም!»

«እኔም እኮ ይህንን መሰሉን ፍቅራችሁን በማየት ነው፥ እንድታርፉና የሰላም ሕይወት እንድትመሩ ሞትን የተመኘሁት።»

በዚያን ጊዜ ነበር ካቲ ፊቷን ወደ እኔ መለስ በማድረግ

«ለምን ትቀልጂያለሽ ጃኒ! ብታምኚም ባታምኚም እግዚአብሔርን በነጋ በጠባ ይመጨቀጭቀው የአንቺን ሞት ከማየቴ በፊት በቅድሚያ እኔን እንዲወስደኝ ነበር።» ብላ ልማደኛ እንባዋን ለቀቀችው።

አሁንም ደግሞ በተራዬ ተለማማጭና አጽናኝ የሆንኩት እኔ ነበርኩ። ስለዚህ ያንን መሰሉን ምኞት ማንጸባረቄ ስሕተት ብቻ

ሳይሆን ኃጢአትም ጭምር መሆኑን በማመን ለካቲ ረጋ ባለ አንደበት ገለጽኩላት። በመጨረሻም ይህን መሰል ርኩስ ተግባር ዳግመኛ በአእምሮዬ እንደማይቀረጽ ከማልኩላት በኋላ ወደ ማረጋጋቱ በመመለስ እንደ በፊቱ ከአጠገቤ ቁጭ አለች፤ ፀጉሬንም እያሻሸችኝ የባጥ የቆጡን ስናወራ አመሸን። የማታ ማታ የተለያየነውም በሣቅና በፈገግታ ነበር። ይሁን እንጂ የካቲ እግር ገና ከመውጣቱ ደግሞ እንደ ልማዱ ስለ ፍቅረኛዬ ስለ ዲክ በማስታወስ ነገሮችን ማውጣትና ማውረዱን ተያያዝኩት። የሚገርመው ግን ልክ መልእክተኛ የተላከበት ይመስል የዲክ በዚያኑ ምሽት ሊጠይቀኝ መምጣት ነው። ገና እንዳየሁትም ዲክ! ስል በቁልምጫ ስሙ ጠራሁት። ወዲያውኑ ደግሞ ያለሁበት ሁኔታ ታውሶኝ እንደዚያ ለመቅበጥ በመሞከሬ እራሴን ታዘብኩት።

እራሱ ግን ሣቅ ብሎ «ተሻለሽ ወይ ጃኒ?» ሲል ከጠየቀኝ በኋላ ከግንባሬ ላይ ሳም አድርጎኝ ተቀመጠ። እኔም እምብዛም ለውጥ አለማየቴን እንደገለጽኩለት ከእጁ የማይለየውን መጽሐፍ ቅዱስ ገልጦ «እስቲ ለማንኛውም የሚከተለውን ጥቅስ ከልብ አድምጪው» ብሎ ያነብልኝ ጀመር።

«ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት። ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም» (ያዕቆብ 1፡2–4)።

እንደ ጨረሰም ቀና ብሎ አየኝ። እኔም በዚያን ጊዜ «እስቲ የጥቅሱን መልእክት አብራራልኝ?» ስል ጠየቅኩት።

«መልእክቱ እንኳን ግልጽ ይመስለኛል። ያም ሆኖ ግን ከአንቺ ሕይወት ጋር ስናዛምደው እግዚአብሔር ለዚህ መሰሉ አደጋ እንድትጋለጪ መፍቀዱ ከበስተጀርባ ለአንድ ትልቅ ዓላማ ስለመረጠሽ መሆኑን ነው የሚያረጋግጥልን፤ ስለዚህ ይህ ፈተና የአንቺን ዕድል ለማጨለም ሳይሆን ለበጎ ዓላማ የታቀደ መሆኑን በመረዳት መንፈሰ ጽኑ ልትሆኚ ይገባል» አለኝ ዓይን ዓይኔን በማበረታታት እያየ።

«እኔም እኮ አልፎ አልፎ ብበሰጫጭም እምነቴ ግን አሁንም በእግዚአብሔር ላይ ነው» ስል መለስኩለት።

«ጥሩ! በዚህ ከተግባባን ከያዕቆብ መልእክት ተከታታዩን አነብልሻለሁ።»

«ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቀፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል» (ያዕቆብ 1፡5-6) አለና አቆመ።

«በል እንግዲህ እግዚአብሔር እንደ ተስፋ ቃሉ እኔንም ከዚህ ከታሰርኩበት በመፍታት እንደ ጓደኞቼ ለመሆን ያበቃኝ ዘንድ ጸልይልኝ» አልኩት።

ዲክ መጽሐፍ ቅዱሱን አስቀምጦ ከአልጋው ሥር ከተንበረከከ በኋላ «አባት ሆይ፥ ለእኛ ለልጆችህ ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ ደኅንነት ስለምታስብና ስለምትጨነቅልን እናመሰግንሃለን። በመጽሐፍ ቅዱስህም ውስጥ ስላሰፈርክልን የመጽናኛ ቃላት እናመሰግንሃለን። ‹እነሆም ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን› ባልከው መሠረት በበጎነትህ ትጎበኘን ዘንድ እንለምንሃለን። ጸሎታችንንም ስማን! በጌታ በኢየሱስ ስም አሜን» አለና ዝም አለ።

ያን ጊዜ እኔም በተራዬ «ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ በጎዘንም ሆነ በመከራዬ ጊዜ ወደ አንተ በማንጋጠጥና እርዳታህን በመሻት ምትክ እራሴን ለብስጭትና ለትካዜ በመዳረጌ ይቅርታ ታደርግልኝ ዘንድ እለምንሃለሁ። የደረሰብኝ አደጋ በእምነቴ እጠነክር ዘንድ ስለመሆኑም እንድረዳ ስላደረግክኝ አመሰግንሃለሁ። በአንተም ፈቃድ ከዚህ ሕመሜ እንደምፈወስ፥ ብሎም በእኔ ላይ በምትፈጽመው ተአምር ብዙዎች ወደ እግዚአብሔር መንገድ እንደሚመለሱ እምናለሁ» ስል የበኩሌን ጸሎት አደረስኩ። ዲክ በዚህ ሁኔታዬ በመርካቱ ለረጅም ሰዓታት ዘና ብሎ ሲያዋራኝና ሲያጫውተኝ አምሽቶ በመሄጃውም ጊዜ እንደ ፍቅረኞች ሁሉ ከንፈሮቼን በመሳም ተሰናበተኝ።

ከዚያን ምሽት በኋላ ባሉት ተከታታይ ቀናት ቅልል እንዳለኝ ነበር የከረምኩት። እንዲያውም ከብርታቴና ከጽናቴ የተነሣ በየተራው ለሚንቀሳቀሱት አስታማሚዎችም ሆነ አልፎ አልፎ ሊጠይቁኝ ለሚመጡት ጓደኞቼ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል እሰብክላቸው ነበር። በእርግጠኝነትም ነበር «በቅርቡ ድኜ እንደ እናንተ በእግሬ ስመላለስ ታዩኛላችሁ!» ስል እናገር የነበረው።

ከዚህም አልፎ ተርፎ ማንኛውንም አሳብ በእግዚአብሔር ላይ እስከመጣል ደርሼ ነበር። ለምሳሌ ወላጆቼ ሊጠይቁኝ መጥተው በነበረበት ዕለት የሆስፒታሉ አስተዳዳሪ ወደ መኝታ ክፍሌ ዘው ብሎ በመግባት አባቴን «ለልጅዎ የሆስፒታል ቆይታዋ ያሲያዙት 30 ሺህ ዶላር እያለቀ ስለሆነ ተጨማሪ ክፍያ ልንጠይቅዎት መገደዳችን ስለማይቀር ከአሁኑ አስቡበት» ሲል ማስጠንቀቂያ ለመስጠት ሞክሮ ነበር። ይሁን እንጂ እኔ ነበርኩኝ በመሸቀዳደም «ስለወደፊቱ

የሚያውቀው አንዱ እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ወላጆቼን ልታስጨንቃቸው አይገባም» በማለት የመለስኩለት። እርሱም በዚህ መሰሉ ልበ ሙሉ አነጋገሬ በመደነቅ መልስም ሳይሰጠኝ ነበር የወጣው።

በሌላ ጊዜ ደግሞ ዶክተር ሼሪል የእኔ ዓይነቱ በሽታ በሕይወት ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ በማንሣት «ከልጅነታቸው ጀምሮ ልዝብና ጭምት ባልሆኑ ሕመምተኞች እምብዛም ለውጥ ባያስከትልም እንደ ጃኒ የመሳሰሉትን ስፖርት አፍቃሪዎች አስተሳሰብና ተስፋ ያጨልመዋል» ሲል ተናግሮ ነበር። ሆኖም ግን ለእርሱም የሰጠሁት መልስ «የቱንም ያህል የከፋ ዕድል የገጠመን ቢመስለን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እስካለ የጨለመውን ያበራዋልና ልንሰጋ አይገባም» የሚል ነበር።

አሁንም በሌላ ጊዜ አንዲት አስታማሚ የምርመራ ውጤት የተዘገበበትን ፋይል እያገላበጠች «በጣም የሚያሳዝነው እኮ! በሦስተኛውና በአራተኛው ደንደስሽ ምትክ የተለያየው ጥቂት ዝቅ ብሎ ያለው ቢሆን ኖሮ ይህን ጊዜ ቢያንስ እጆችሽን እንደ ልብ ልታላውሺያቸው በቻልሽ ነበር» ስትል ተችታ ነበር። ሆኖም ለእርሷም ቢሆን የሰጠኋት መልስ «አንቺ እንዳልሺው ሳይሆን የተለያየው የሰውነቴ ክፍል አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ በአራተኛውና በአምስተኛው ደንደሴ መሀል ያለው ቢሆን ኖሮ ይህን ጊዜ ሞቼ ነበር ማለት አይደለም? ስለዚህ በዚያው ደረጃ በመገታቱ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባው» በማለት አፍዋን አስይዤ ነበር የመለስኳት። ዲክ ሊጠይቀኝ ተመልሶ በመጣበት በዚያኑ ሰሞን ጎላ ባሉ ፊደሎች የተጻፈ መጽሐፍ ቅዱስ በስጦታ መልክ አበረከተልኝ፤ ምክንያቱም አልጋው በደረቴ ሲገለብጠኝ መጽሐፉን ወለሉ ላይ አድርጎ የሚገልጽልኝ ሰው ካለ ማንበብ ስለምችል ነው። የሚከተለውን መልእክት አስፍሮበታል፦

«እጅግ ለማፈቅርሽ ጃኒ

ጳውሎስ በሮሜ 8፡28 ላይ እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን» የሚል የተስፋ ቃል እንዳሰፈረልን ሁሉ ክርስቶስ ከሁላችንም እንዳይለይና ምኞታችንንም ለፍሬ እንዲያበቃልን የምንጊዜም ጸሎቴ ነው»

ያንቺው ዲክ

መስከረም 9 ቀን 1967»

በዚህ አጋጣሚ ያልተረዳሁት ነገር ቢኖር ይህ መልእክት የዲክን የመሰናበቻ ቃላት ያዘለ መሆኑን ነው። ምክንያቱም ዲክ ወዲያውኑ ነበር ከፍተኛ ትምህርቱን ለመከታተል ኮሌጁ ወደሚገኝበት ከተማ

የሄደው። ይሁን እንጂ ለመጨረሻ ጊዜ ከመሰነባበታችን በፊት «ታፈቅረኛለህ ወይ ዲክ?» ስል ጠይቄው ነበር።

እርሱም «ምን ጥርጥር አለው!» በማለት ነበር የመለሰልኝ። እኔም «የለም ደግመህ ደጋግመህ ‹አፈቅርሻለሁ› ስትል ግለጽልኝ እንጂ!» በማለት ሙዝዝ ብዬበት እንደነበር ትዝ ይለኛል። እርሱም «አፈቅርሻለሁ! አፈቅርሻለሁ!» ባለ ቁጥር ከንፈሬን እየሳመ እንደነበር አይዘነጋኝም።

ቀጠል በማድረግም ዛሬም እንደ ድሮው ከእኔ በስተቀር ሌላ ሚስት እንደማታገባ ቃል ትገባልኛለህ? ብዬው ነበር።

«አዎን! ቃል እገባልሻለሁ»

«እሺ የሆነስ ሆነና መቼ ነው የምንጋባው?»

«ያው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ከሆስፒታል እንደ ወጣሽ ይሆናል!»

የዚያን ሌሊት ጸሎቴ ደግሞ ከምንጊዜም ለየት ብሎ እግዚአብሔርን የዲክ ሚስት ለመሆን ያበቃኝ ዘንድ በመነዝነዝ ላይ ያተኮረ ነበር። ለዚህ ግን ወሳኞቹ ሁለት ነገሮች ለመሆናቸው አልተረሳኝም . . . . . የእኔ ካጥመለመለኝ ሽባነት መፈታትና የዲክ ፍቅር አለመክሰም!!!

ከግሪን ኦክስ ሆስፒታል የመጣችው ባለሙያ ወጌሻ እንድታየኝ በማስፈለጉ ነበር በማግሥቱ በሚገፋ ጋሪ ላይ አድርገው ወደ ሌላ ክፍል የወሰዱኝ። እዚያም ደርሼ ከአንድ ደረቅ ጠረጴዛ ላይ ካስተኙኝ በኋላ ከክርንና ከርኔ ላይ በመጠፍነግ አሰሩኝ። ከዚያም እንግዳዋ ወጌሻ ወደ እኔ ጠጋ በማለት «በቅድሚያ ልናደርግልሽ ስላቀድነው ለየት ያለ የሕክምና እርዳታ አንዳንድ መመሪያዎች ልሰጥሽ ስለሆነ በጥንቃቄ እንድታዳምጪኝ ላሳስብሽ እወዳለሁ» ብላ ይበልጥ ቀረብ ካለቺኝ በኋላ፥ «ከአሁን በፊት እንደተገለፀልሽ ሁሉ ከሰውነትሽ ውስጥ አደጋ የደረሰበት አራተኛውና አምስተኛው የደንደስ አጥንትሽ መገናኛ ላይ ነው። ምናልባትም አደጋው ከዚያን ከፍ ባሉት የደንደስ መገጣጠሚያዎችሽ ላይ ደርሶ ቢሆን ኖሮ ይህን ጊዜ አዕምሮሽ ደንዘ የልብ ምትሽ ቀንሶ እስከ ሞት ባደረሰሽም ነበር። ዳሩ ግን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባውና የአንቺ ጉዳት ግን ለጥቂት ዝቅ ባለው መገጣጠሚያሽ ላይ በመሆኑ እጅና እግሮችሽን በማደንዘዝ ላይ የተገደበ ሆነ። ከዚህም በተጨማሪ በአንገትሽና በትከሻችሽ ደም ሥሮች ከመጠነኛ ጉዳት በስተቀር የጎላ ተጽዕኖ የለም።

«አሁንም ቢሆን በበኩላችን የምንጥረው የሚታየን የተሰፋ ጭላንጭል ቢያንስ እጆችሽን አንድ ቀን ልታንቀሳቅሺያቸው እንደምትችዪ ነው። ይህ ደግሞ የአንቺን ያላሰለሰ ብርታትና ቆራጥነት የሚጠይቅ ነው። ምክንያቱም እኛ በምንሰጥሽ ምክር መሠረት

ከንዶችሽንና እጆችሽን ለማላወስና ለማንቀሳቀስ መጣርና መፍጨርጨር ስላለብሽ ነው» ብላ ሁኔታዬን ለማጤን ያህል ትኩር ብላ አየችኝ።

እኔም በዚያን አጋጣሚ በመጠቀም «በእርግጥ የመዳን ተስፋ አለኝ ሲስተር?» ስል በመጓጓት ጠየቅኳት። «አዎን ተስፋ አለሽ! በምርመራ ውጤትሽ ላይ እንደሠፈረው ዘገባ በማጅራትሽም ሆነ በትከሾችሽ አካባቢ ያሉትን ደም ሥሮችሽን የማንቀሳቀስ ሃምሣ በመቶ ዕድል እንዳለሽ ነው። ስለዚህ ቀስ በቀስ ከንድና ክርኖችሽን ከዚያም ወረድ በማለት ወርችችሽንና የእጅ መዳፎችሽን ለማላወስ የምትችዪበት ጊዜ ሊመጣ ይችላል። በመሆኑም ከቅርብ ጀምሮ የተቆጣጠሩት ደም ሥሮችሽ እንዲፍታቱ በሠለጠኑ ወጌሻዎች እርዳታ ይደረግልሻል። አንቺም መንፈስ ብርቱ በመሆን በሚያዙሽ ሁሉ እንድትተባበሪያቸው!»

«እሺ እተባበራለሁ!»

«ጥሩ በይ እስቲ ሙከራችንን አሁኑኑ እንጀምረውና እስቲ በቅድሚያ ከማጅራትሽ ቀና በማለት ትከሻዎችሽን ልታንቀሳቅሺያቸው ሞክሪ?»

«አስታማሚዋ እንዳዘዘችኝ ለመፈጸም ጥርሶቼን ነክሼ ተፍጨረጨርኩ። ይሁን እንጂ ከጭንቅላቴ በታች ያለው የአካል ክፍሌ ቅንጣት ያህል ሊንቀሳቀስልኝ አልቻለም።» እርሷም በመደጋገም ያደረግኩትን ጥረት ፍሬቢስነት እንዳጤነች ጎንበስ ብላ ማጅራቴን ደገፍ በማድረግ ደጋግማ መለስ ቀና ካደረገችኝ በኋላ «አየሽው ማጅራትሽን ማላወሱ የቱን ያህል ቀላል እንደሆነ» በማለት ልታደፋፍረኝ ሞከረች።

እኔም ከዚያን በኋላ መንፈሴን በማጠናከርና ያለ የሌለኝን ኃይል በማሰባሰብ እንደ ምንም በድጋሚ ታገልኩ። እንደ አጋጣሚም ስንዝር ያህል ቀና ለማለት በመቻሌ አስታማሚዋ በደስታ እየተፍነከነከች «ጎበዝ ልጅ ጃኒ! ጎበዝ!» ስትል አጨበጨበችልኝ። ትንፋሼም ትንሽ መለስ ማለቱን እንዳየች ያንን ልምምድ ደጋግሜ እንድሠራው አበረታታችኝ። ከዚያም ቀጥላ ትከሻዬን ላላውሰው እንድሞክር ገፋፋችኝ። ይህም ሲሆን እንደበፊቱ በጣርና በጭንቅ በመፈጸሜ አሁንም አድናቆቷን ከገለጸችልኝ በኋላ «የዛሬው ሙከራችን እጅግ የሚያበረታታ ነው። በመሆኑም ያለምንም መቦዘን ሳታቋርጪ ልትገፊበት ይገባል። በዚህም ይዞታ ከቀጠልሽ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከንዶችሽንም ሆነ እጆችሽን ልታንቀሳቅሺያቸው እንደምትችዪ ሙሉ እምነቴ ነው። ሰሞኑን ወደ ግሪን ኦክስ ሆስፒታል ተዛውረሽ በዚያ የቅርብ ክትትል እንዲደረግልሽ ሁኔታዎችን አመቻቻለሁ» በማለት ቃል ገብታ ተሰናበተችኝ።

ምዕራፍ አራት

እኔም በወጌሻዋ አንደበት እንደተፈነጠቀልኝ ተስፋ በእግሮቼ የምራመድባቸውና በእጆቼም የምሠራባቸው ቀናት ይመጡ ይሆናል በማለት ወደ ግሪን ኦክስ ሆስፒታል የምዛወርበትን ዕለት በጉጉት ስጠብቅ ቆየሁ። ያም ቀን ሳይታሰብ ፈጥኖ በመድረሱ የለመድኳቸው ሐኪሞችና አስታማሚዎች ሞቅ ያለ ሽኝት ነበረ ያደረጉልኝ። ከዚያን ዕለቱም የመሰነባበቻ ቃላት በተለይ ዶክተር ሃሪስ «ከእንግዲህ ጃኒ ጠንቃቅ ሰብሰብ ማለት አለብሽ! በተረፈ ግን እንደ ልማድሽ በየምሽት ክበቡና በየፓርቲው እየዞርኩ እጨፍራለሁ ብትዪ መልሰን ነው የምናመጣሽ!» ሲል የወረወረው የፌዝ ማስፈራሪያ የማይረሳኝ ነው።

እኔም ብሆን በተራዬ ፌዙን በፌዝ ለመመለስ «በምን አቅማችሁ ነው ወደዚህ የምትመልሱኝ? አንድ ጊዜ እግሬ ከዚህ ግቢ ወጣ ይበል እንጂ አባራችሁም ልትይዙኝ አትችሉም» በማለት አሳቅኳቸው።

ወደ አምቡላንሱ የወሰዱኝ አኒታና አሊስ የተባሉት ሁለቱ አስታማሚዎች ሲሆኑ እነርሱም የኋላ ኋላ በቁርጥ ልለያቸው መሆኑን በማወቅ በእጅጉ አዝነው ነበር።

ከሆስፒታሉም እንደወጣን ለመጀመሪያ ጊዜ ንጹሕ አየር በመሳቤና የፀሐይዋም ሙቀት በሰውነቴ ላይ በማረፉ ልዩ አድናቆትና ደስታ ነበረ ያደረብኝ። ይሁን እንጂ ከአዲሱ ከግሪን ኦክስ ግቢ ደርሰን በዚያው በሚገፋ ጋሪ ወደ መኝታ ክፍሌ በወሰዱኝ ወቅት ያው የዱሮው የትካዜ ስሜት ወርሮኝ ነበር። ከተዘጋጀልኝ መኝታ ቤት ገና ከመግባቴም ግራና ቀኙን መማተር ጀመርኩኝ። ከእኔ በስተቀር ሌሎች አራት ሕመምተኞች በክፍሏ ውስጥ እንደሚገኙ እንዳጤንኩም «የእኔ ስም ጃኒ ኢሬክሰን ይባላል» በማለት እራሴን አስተዋወቅሁ። አንደኛዋም ከአፌ ቀበል በማለት «ጃኒ ከሚሉሽ ለምን እንደመልክሽ ቁንጅና «ጆሊ» /ውቢት/ አይሉሽም ነበረ» ብላ ሁላችንንም አሳቀችን።

ከዚያም ሌላዋም እንዲሁ በተራዋ «የክበባችን አባል ለመሆን በመብቃትሽ ዕድለኛ ነሽ» ስትል ካሳሳቀችን በኋላ በቅድሚያ እራሷን ቤቲ ጃክሰን እባላለሁ ስትል አስተዋወቀችኝ። በማከታተልም ከበራፉ አጠገብ ወደተኛችው ልጅ በማመልከት «እርስዋ ደግሞ ስመ ሞክሼዬ ቤቲ ግሎቨር ወይም ቢ.ጂ. በመባል የምትታወቀው ስትሆን፥ ከእርሷ ቀጥሎ ያለችው ዴኒስ ትባላለች። ከሁላችንም በመሽቀዳደም ያናገረችሽ ደግሞ አንዊልሰን ናት። በተጨማሪ የክበባችን ፕሬዚዳንት እርሷ መሆኗን ልገልጽልሽ እወዳለሁ» አለችና ሳቅ አለች።

በዚያን ጊዜ አን ሲጋራ ለኩሳ ክፍሉን በጭስ አፍናው ስለነበረ እኔም አፌ ላይ እንዳመጣልኝ «ለጤናሽ እኮ ጎጂ ነው» ስል ለመተቸት ሞክሬ ነበረ። ሆኖም «የአልጋ ቁራኛ ሆኜ ረጅም ዕድሜ ከማሳለፍ ዕለተ ሞቴን አፋጥኜ ቶሎ ለመገላገል ስል የማደርገው ነው» በማለት ያልጠበቅኩትን መልስ ሰጠችኝ። ታዲያ እንደዋዛ የወረወረችው ይህ አነጋገሯ እኔንም ቢሆን ውስጥ ውስጡን ሳይከነክነኝ አልቀረም። በተለይም በአንድ ወቅት የእንቅልፍ ክኒኖች በመዋጥ እራሴን ለመግደል የመመኘቴም ጉዳይ ሳይታወሰኝ አላለፈም። ስለዚህ የሁላችንንም የሆደ ባሻነት ስሜት በሆዴ በማጤን ለአን ተቃውሞ ሳይሆን ፈገግታ በመለገስ «በርቺና ግፊበት» አልኩና በተራዬ አሳቅኳት።

በመቀጠል ደግሞ ወደ ቢ.ጂ አየት በማድረግ ነበረ «ለመሆኑ ከዚህ ሆስፒታል ከገባሽ ምን ያህል ጊዜ ይሆንሻል?» ስል ጥያቄ ያቀረብኩላት።

እርሷ ግን «ሁለት ዓመት ያህል ናት! ስትል እንደ ቀልድ መለሰችልኝ።

በዚያን ጊዜ የታየኝ የእራሴው የወደፊት ዕድል ነበረ። እኔ በሁለት ወራት ውስጥ ያንን ያህል እንዳላማረርኩ ቢ.ጂ ግን በዓመታት ቆይታዋ በማሾፍዋ በአንድ በኩል በመንፈስ ጥንካሬዋ እንድቀና ሲያደርገኝ በሌላ በኩል ድክመቴን ለመገንዘብ አስችሎኛል። ከእንግዲህም ተስፋ ላለመቁረጥ ትልቅ ትምህርት ነበረ ያገኘሁበት። በመሆኑም ከዚያን ዕለት ጀምሮ አብረውኝ ለሚጨነቁትና ለሚጠበቡት ወላጆቼም ሆነ ወዳጆቼ የተኮሳመነ ፊት ላላሳያቸው ከውሳኔ ላይ ደርሼአለሁ።

እንደ አጋጣሚም በማግሥቱ ጧት ላይ ካቲ ልትጠይቀኝ እንደመጣች ያቀረብኩላት ጥያቄ ቢኖር ያንን የቀመቀመውን ፀጉሬን እንድታጥበኝና ፊቴን ወላውላ እንድታሰማምረኝ ነበረ። ምክንያቱም ወላጆቼ በሚመጡበት ሰዓት ከወትሮው በተለየ መልክ እንዲያዩኝና መንፈሳቸው እንዲታደስ ነው። ይሁን እንጂ ኪቲ በዚያን ዕለት የእኔን ፀጉር ብቻ ሳይሆን የአራቱን የክፍል ጓደኞቼን ፀጉር ማጠብ ነበረባት። እርሷም ባለመሰልቸት በማንቆርቆሪያ ውኃ እያመላለሰች ስታጣጥበንና ስታስማምረን ዋለች። ከዚያን ዕለት ጀምሮ የክፍላችን ሕይወት ነፍስ እንደ ዘራና ደስታን እንደ ተላበሰ ነበር የሚውልና የሚያድረው። በየቀኑ ለተወሰኑ ሰዓታት ጎብኚዎች እንዲያዩን ቢፈቀድም ከዚህ በተረፈ ግን ስናወራና ስንቃለድ እንውላለን። እርግጥ ለአምስታችንም ቢሆን ከተኛንበት በማንጋጠጥ ቴሌቪዥን ለመከታተል የሚያስችለን መስታወት በየፊናችን ተተክሎልን ነበር። ከዚህ ውጪ የነበረን ዕድል

ግን እነኛ የሠለጠኑት ወጌሾች ወደሚገኙበት ክፍል ለተወሰኑ ሰዓታት በመወሰድ ገላችንን በቅባቶች መታሸት ብቻ ነው። እርግጥ አልፎ አልፎ እጅና እግራችንን፥ ጀርባችንንና ማጅራታችንን በኤሌክትሪክ ሽቦዎች እያሞቁ ቆልመም ዘርጋ፥ ጎበጥ ቀና በማድረግና አልፎ አልፎም በሰንሰለቶች በመወጣጠር ያስጨንቁን ነበር።

ታዲያ እንዲህ የምታሠቃዩን ለምንድን ነው? ብለን ስንጠይቃቸው የሚሰጡን መልስ ምን ጊዜም ቢሆን ደም ሥራችሁ እንዲፍታታና እንዲ ልብ ደም እንዲያዘዋውር ነው የሚል ነው። ይህም አልበቃ ብሎ ቢያንስ ለአንድ ሰዓት ያህል ከተሽከርካሪ ወንበር ጋር ታስረን ያለ ደጋፊ ቁጭ እንድንል ይደረግ ነበር። ታዲያ ለእኛ ለዚያ ክፍል ጓደኛሞቹ ለተወሰነ ጊዜ ሆድ የሚያስብሰንና የሚያበሳጨን ነገር የመለያየታችንና ለአንዳንድ ሥቃዮች የመዳረጋችን ጉዳይ እንጂ ቀስ በቀስ በማስመዝገብ ላይ የነበርነውን አካላዊ ለውጥ አላጤንነውም ነበር። ለምሳሌ እኔ በክርኔና በደረቴ ውስጥ ያሉት ደም ሥሮች መንዘር ለመጀመራቸው ያንንም ያህል ደንታ አልሰጠሁትም። ታዲያ በእንዲህ ያለው ሁኔታ ላይ በነበርኩበት ወቅት ነበር የምወዳት ጓደኛዬ ዲያና ልትጠይቀኝ የመጣችው። እርሷም ስለ አንዳንድ ነገሮች ስታጨዋውተኝ ከቆየች በኋላ ምንጊዜም ከእጇ የማይለየውን መጽሐፍ ቅዱስ ከፈት በማድረግ የሚከተለውን ጥቅስ አነበበችልኝ።

«በዚያን ቀንም ከእኔ አንዳች አትለምኑም። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል። እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ» (ዮሐንስ 16፡23-24)።

እንደ ጨረሰችም «ባነበብኩልሽ መልእክት ታምኚበት የለም?» ስትል ጠየቀችኝ።

«አዎን አምንበታለሁ! እግዚአብሔር አንድ ለየት ያለ ዕድል እያዘጋጀልኝ ለመሆኑም አልጠራጠርም» ብዬ መለስኩላትና ቀጠል በማድረግም «ለመሆኑ በቤተ ክርስቲያናችን ምን እያዘጋጁ እንደሆነ ሰምተሻል?» ስል ጠየቅኳት።

«በየት? በእኛ ቤተ ክርስቲያን?» አለችኝ መለሰችና።

«አዎን! በእኛ ቤተ ክርስቲያን»።

«የለም ምንም ነገር አልሰማሁም»።

«ቤተ ክርስቲያኒቱ ለእኔ ስትል የአንድ ቀን ጸሎት ለማድረግ ወስናለች አሉ። እግዚአብሔር ከሕመሜ ይፈውሰኝ ዘንድ ሊያድሩ ነው» አልኳት።

«ኡ ይሄማ ትልቅ ነገር ነው! በዚህ ላይ እንግዲህ የአንቺም ልመና ከተጨመረበት በቅርብ ጊዜ ውስጥ እንደምትፈወሺ አትጠራጠሪ።»

እውነትም በዚያኑ ደቂቃ የጣቶቼ ጫፎች ደም ሲነዝሩ የተሰማኝ ስለመሰለኝ እግዚአብሔር ፈውሱን ከዚያችኑ ደቂቃ የጀመረ ያህል ነበረ እምነቴ የበረታው። በቤተ ክርስቲያን ጸሎት በተደረገልኝ ሌሊት ከሰበካው ጉባዔ አባላት በተጨማሪም የትምህርት ቤት ጓደኞቼና አስተማሪዎቼ ሁሉ እንደተገኙ ካቲ ገልጻልኛለች። የብዙዎቹ እምነት በዚያኑ ሌሊት ከሕመሜ ሁሉ ተገላግዬ እንደማድር ቢሆንም ዳሩ ግን እግዚአብሔር የወሰነው ጊዜ አልደረሰም ነበረና ያው እንደ ዱሮዬ ከአልጋ ላይ እየተጋደምኩ መዋል ነበረብኝ። ያም ሆኖ ግን በአምላኬ ላይ ያለኝ እምነት ዝንፍ ባለማለቱ ብዙዎቹ ጠያቂዎቼ የእምነቴን ጽናትና ቆራጥነት በማንሣት ያመሰግኑኝ ነበር።

ምዕራፍ አምስት

ሆስፒታል ከገባሁ ወደ ዓመት ሊሞላኝ የተቃረበ ቢሆንም ለተወሰኑ ደቂቃዎች እራሴን ችዬ ለመቀመጥ ከመብቃቴ በስተቀር ሌላ ጉልህ የሆነ መሻሻል አልታየብኝም ነበር። ከዚህ በተጨማሪም ደግሞ ተኝቼ የምውልበት የጀርባዬ ቆዳ እያኮፈኮፈ ለሥቃይ ዳርጎኝ ነበር። ያም ሆኖ ግን ወርሃ ታኅሳስ ገብቶ የገና በዓል እየተቃረበ በመሄዱ ለአንድ ቀን ወደ ወላጆቼ ዘንድ በመሄድ ዕለቱን አብሬያቸው እንድሳልፍ ተፈቅዶልኝ ነበር።

ያም ቀን ደርሶ አባቴ መኪናውን ይዞ ከውጪ ሲጠባበቅ፥ ካቲ ግን ወደ መኝታ ክፍሌ በመዝለቅ ገላዬን ስታጣጥብ፥ ፀጉሬን ስታበጣጥርና ስታሰማምረኝ ብዙ ጊዜ ፈጅች። በመጨረሻም እጅግ እወደው የነበረውን ቀሚሴን አጥልቃልኝ ምን እንደምመስል እንዳየው በመስታወት ከፍና ዝቅ እያደረገች ከላይ እስከ ታች ሰውነቴን አስቃኘችኝ። እርግጥ ሰውነቴ ለመኮሳመኑና ጉንጮቼ ለመጣበቃቸው አሌ ባይባልም፥ በተለይ ቅር ያሰኘኝ የፀጉሬ እንደ ድሮው አለመዘናፈል ነበረ። ይህንንም ለካቲ ስለገለጽኩላት እርሷው ትጠቀምበት የነበረውን ወርቃማ የፀጉር ዊግ በማውለቅ አጠለቀችልኝ። በዚህም መልኩ ካማርኩና ከተጋጊያጥኩ በኋላ ነበር ሁለት ወንድ አስታማሚዎች የሳንሳ በመሸከም ወደምትጠብቀኝ መኪና የወሰዱኝ። ከኋላ መቀመጫውም ላይ በጥንቃቄ ካሳረፉኝ በኋላ ደረቴን ለአደጋ መከላከያ በተዘጋጀው ሽራ አሰሩኝ። እንደዚሁም መኪናዋ በኩርባዎች ላይ በምትጠመዘዝበት ጊዜ ላልታሰበ ድንጋጤና የደም ሥር መኮመታተር እንዳልጋለጥ እጎቴ ካቲ ከጎኔ በመቀመጥ እንድትደግፈኝ አደረጉ።

እቤት እንደደረስኩ ሞቅ ደመቅ ያለ አቀባበል ነበረ የተደረገልኝ። እኔም ከዓመት በኋላ ወደዚያ ተወልጄ ወደአደግኩበት ቤት ለመመለስ በመብቃቴ ለአምላኬ ልዩ ምስጋና አቀረብኩ። ያም ሆኖ ግን ወላጆቼ እንዳርፍበት ያዘጋጁልኝ የቀድሞውን መኝታ ክፍሌን ሳይሆን የምግብ ቤቱን ነበር። ይኸውም የመኝታ ክፍሌ የሚገኘው ፎቁ ላይ ስለነበር ደረጃዎችን በሽከም እንዳልወጣና እንዳልወርድ በማሰብ መሆኑ ገብቶኛል። ምናልባትም ትንሽ የተሰማኝ ቅሬታ ቢኖር ከዚያ ከምግብ ቤቱ ውስጥ በተዘረጋልኝ አልጋ ላይ ጭኖቼን አንፈራጥጬ የመቀመጡ ጉዳይ ነው።

ለዚህም ነበረ እናቴን «እባክሽን ብርድ ልብሱን አልብሺኝ?» ስል ጠይቄአት የነበረው።

እርሷ ግን በነገር አካሄዴ ባለመጠራጠር «ምን ነው በረደሽ እንዴ ጃኒ?» ስትል ጠየቀችኝ።

«አይ! መብረድ እንኳን በርዶኝ ሳይሆን እየተመላለሱ የሚጠይቁኝ እንግዶች በድኑን እግሬን እንዳያዩት ብዬ ነው» አልኳት።

«እግርሽ እኮ ቢታይ እንደ ድሮው ያምራል እንጂ ምንም ለየት ያለ ምልክት አይታይበትም።» ብላ ወደ ካቲ አየት በማድረግ እውነቴን አይደለም እንዴ? ስትል የድጋፍ አስተያየት ጠየቀቻት።

ካቲም ፈጠን በማለት ነበረ «እንዲያውም ለጃኒ የሚያስታውቅ መስዓት እንጂ እግሮቿስ ከድሮው በምንም አይለዩም» ስትል የተናገረችው። ያም ሆኖ ግን የግድ ብርድ ልብስ እንዲያለብሱኝ ካደረግሁ በኋላ ዘና ብዬ ቀኑን ሙሉ ስጫወት ዋልኩኝ። ምሽቱንም ከወላጆቼና ከእኅቶቼ ጋር የልደት መዝሙሮችን በመዘመር በደስታና በፈንጠዝያ አሳለፍነው። ከዚያም ወደ እኩለ ሌሊት ሊቃረብ ሲል ሁላችንም እንቅልፋችን መጣ። አባትና እናቴ ወደ መኝታ ክፍላቸው ሲሄዱ ካቲ ግን ከጎኔ የመንገደኛ አልጋ ዘርግታ ተኝታ ነበር። የሰላም እንቅፍል እንዲያሸልበኝ በማለት ከሰቆቃው ኤርምያስ የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብባልኝ ነበር። እኔም በየጥቅሶቹ መሀል አንዳንድ አሳቦችን በአዕምሮዬ ማውጠንጠኔ አልቀረም። ከእኔም ሕይወት ጋር የሚመሳሰልበትን በየጥቅሱ ማብቂያ እያብሰለሰልኩ ነበረ።

«በሌሊት እጅግ ታለቅሳለች፥ እንባዋም በጉንጭዋ ላይ አለ፤

ከውሽሞችዋ ሁሉ የሚያጽናናት የለም፤

ወዳጆችዋ ሁሉ ወነጀሉአት ጠላቶችም ሆኑአት።

> አቤቱ የእኔ ጌታ ይህ አባባል የቱን ያህል ትክክል ነው። ስለምን እንባዬን በእጆቼ መጥረግ እያቃተኝ በጉንጮቼ ላይ ተዝረክርኳልና!

«ስለ ኃጢአትዋ ብዛት እግዚአብሔር አስጨንቆአታልና»

> አዎን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመተላለፍ ከአንድ በላይ ፍቅረኞች ይዤ ነበረና ቅጣቱ ይገባኛል።

«በእኔ ላይ እንደተደረገው እንደ እኔ መከራ የሚመስል መከራ እንዳለ ተመልከቱ፥... እዩ። ለእግሬ ወጥመድ ዘረጋ ወደ ኋላም

መለሰኝ፥... የኃጢአቶቼ ቀንበር በእጁ ተይዛለች፤ ታስረው በአንገቴ ላይ ወጥተዋል፤ ጕልበቴንም አደከመ»

እንደ እኔስ ለቅጣትና ለፍዳ የተደረገ ማን አለ?

አምላኬስ ለምን እንዲህ ጨከነብኝ?»

«..... በከተማ ጎዳና

..... እንደ ተወጋ ሰው በዛሉ ጊዜ»

እኔ ዘልዬ ከባህር ውስጥ በመግባቴ ለሽባነት ተዳረግሁ.....

«ዘወትር ቀኑን ሁሉ እጁን በላዬ መለሰ።»

ንዴት .....

ተስፋ መቁረጥና ፍርሃት

ሥጋዬንና ቁርበቴን አስረጀ አጥንቴን ሰበረ

የጆርባዬ መላላጥ ለተደጋጋሚ ቀዶ ጥገና መጋለጤ

«ቅጥር ሠራብኝ በሐሞትና በድካምም ከበበኝ።»

አልጋዬ በሽራ ድንኳን የተሸፈነው። ከድካሜም የተነሣ ሽንቴን እንኳን የምፀዳዳው በሣህን ላይ ነው።

«ቀድሞ ሞተው እንደነበሩ በጨለማ አኖረኝ።»

እነሆ የአልጋ ቁራኛ ሆኜ ሞቴን በመጠባበቅ ላይ ነኝ።

«እንዳልወጣ በዙሪያዬ ቅጥር ሠራብኝ ሰንሰለቴን አከበደ።»

እኔም በወጥመድ እንደተያዘች እንስሳ እግርና እጆቼ

ታሥረዋል፤ እርግብግቢቴም በሽቦ ተወጥሯል።

«በጠራሁና በጮኽሁ ጊዜ ጸሎቴን ከለከለ።»

እግዚአብሔር ጨካኝ ኖሯልን?

«ነፍሴን ከሰላም አርቀህ፤ በጎ ነገርን ረሳሁ።»

ለፍጥረታቱም አያስብምን?

(ሰቆቃው ኤርምያስ 1፡2፥ 5፥ 12-14፤ 2፡11፤ 3፡3-8፥17)

የገናን በዓል ከወላጆቼ ጋር በሰላም ላሳልፍ እንጂ ወደ ሆስፒታሉ ስመለስ ደግሞ ያው የቀድሞው የተጠናወተኝ ጎዘንና ትካዜ አልፎ አልፎ ሳይነበንኝ የዋለበት ዕለት የለም። ከዚህም የተነሣ ፍቅረኛዬ ዲክና ጓደኛዬ ዳያና ከመጽሐፍ ቅዱስ በመጥቀስ ይለግሡኝ የነበረው ምክርና ያካፍሉኝ የነበረው የማጽናኛ ቃል ሁሉ ከሕሊናዬ የሚሠወርበት አጋጣሚ ነበረ።

በዚያ ላይ ደግሞ አንዳንድ ሳይታሰብ የሚደርሱ ገጠመኞች ለባሰ ንዴትና ብስጭት ይዳርጉኝ እንደነበረ የማልረሳው ነው። ለምሳሌ የገናን በዓል ከወላጆቼ ጋር አሳልፌ በተመለስኩበት በዚያኑ ሰሞን ባርባራ የምትባለዋ አስታማሚ በማያገባት ገብታ ከታላቅ ብስጭት ላይ ጥላኝ ነበር። ይኸውም ተረኛ በነበረችበት ዕለት ከራስጌዬ የነበረውን ኮመዲኖ ከፋፍታ በምታጸዳበት ጊዜ እንደ አጋጣሚ የዲክን ፎቶግራፍ አግኝታ ኖሮ በዚያኑ ሳቢያ የተፈጠረ ግጭት ነው።

ባርባራ ፎቶግራፉን ብድግ አድርጋ ወደ እኔ አስጠግታ በማገላበጥ «ይሄ ደግሞ የማን ፎቶግራፍ ነው?» ስትል ጠየቀችኝ።

«የዲክ ነው» አልኳት።

«ምንሽ ነው እርሱ?» ስትል አሁንም ጠየቀችኝ።

እኔም ምናልባት መልኩ እንደ እኔ ደስ ብሏት ይሆናል በሚል ግምት ፈገግ እያልኩ «ፍቅረኛዬ» ስል መለስኩላት።

«ፍቅረኛዬ? የማን? የአንቺ ፍቅረኛ?» አለችኝ ድምጽዋን በአግርሞት ከፍ አድርጋ።

«አዎን! የእኔ ፍቅረኛ ነው።»

«ድንቄም ፍቅረኛ እቴ ይህን የአገር ምድሩን ልጃገረድ ያበላሽ ዱርዬና ወንበዴ ነው ፍቅረኛዬ የምትዪው?»

«ይቅርታ የእኔ እመቤት! ምናልባት ተሳስተሽ ወይም እርሱን የሚመስል ልጅ አይተሽ ይሆናል እንጂ ዲክ እንኳን ተብሎለት ያለቀ ጨዋና ቁም ነገረኛ ልጅ ነው» ስል ረጋ ብዬ መለስኩላት።

እርሷ ግን አመጣጧ ለነገር ይመስል አሁንም ንትርኳን ባለመግታት «ኧረ ይሄንን እራሱን ከስንቱ ልጃገረድ ጋር ነው ያየሁት! የለየለት ዘልዛላ አይደለም እንዴ!» አለችኝ መልሳ።

«ኧረ በእግዚአብሔር ይሁንብሽ የእኔ እመቤት! እርሱስ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ አቀርቅሮ ከመዋል በስተቀር የሴት አምሮት የተጠናወተው አይደለም።»

«ድንቄም መጽሐፍ ቅዱስ አንባቢ! ዳሩ ግን አነበበ አላነበበ ይሄ እግዚአብሔር የሚባለው የት አለና! ሁላችሁም ብትሆኑ ስሙን የምትጠሩት ለማስመሰል ያህል ነው እንጂ እግዚአብሔር ፈጣሪ የሚባል ነገር እኮ የለም!» ብላ ወደ አልታሰበ አቅጣጫ መራችኝ።

እኔ ግን እራሴን በመቆጣጠር «ምናልባት ለአንቺ የሌለ ይምሰልሽ እንጂ ለእኔ ግን እግዚአብሔር አለ፤ እውነተኛና ሕያው አምላክ ነው» ስል በተረጋጋ አንደበት መለስኩላት።

«ታዲያ አለ ብለሽ የምታምኚበት ከሆነ ለምን ከባህር ውስጥ ዘለሽ ስትገቢና አንገትሽ ተቆልምሞ ሲቀር ዝም አለሽ? ቢያንስ ተይ አትዝለዪ ብሎ አያስጠነቅቅሽም ነበረ? ወይም ከሆነ በኋላ እንኳን ለምን እንደዚህ ተጥመልምለሽ ስትቀሪ ዝም አለሽ? አያድንሽም ነበር!» አለችና ጮኸችብኝ።

በዚህን ጊዜ ምንም መልስ ልሰጣት ባለመፈለጌ ከአፌ መቆጠቡን መረጥኩኝ። ዓይኖቼም እንዳያዩዋት ስል ከደን አደረግኋቸው። በዚያኑም ቅጽበት ምን ስሜት እንዳደረባት አላውቅም፤ ሆኖም ባለ በሌለ ኃይሏ ተጠቅማ አልጋው ላይ በደረቴ ገለበጠችኝ። እንደ አጋጣሚም አንዱ ክንዴ ከአልጋው ጠርዝ ጋር በመጋጨት ቆስሎ ኖሮ ደሜ ይፈስ ጀመር። እርሷም ለይስሙላ ያህል ቁስሉን በጥጥ ከጠራረገችልኝ በኋላ «ይኸውልሽ የአንቺ እግዚአብሔር! እርሱ እንደሆነ አንገትሽ ቀርቶ ክንድሽም ቢቆለመም ደንታውም አይደለም! ብላ እየሳቀችብኝ ሄደች። እርግጥ እኔም ሆንኩኝ ከአጠገቤ የነበሩት እነ ቢ.ጂ.ና ኦን- በአስታማሚዋ ብልግናና ድፍረት በመናደድ በማሥቱ ለሚመጣው ተረኛ ሐኪም ለመክሰስ ወስነን ነበረ። ሆኖም ግን የዚህ መዘዝ እኔንም ሆነ ጓደኞቼን ለባሰ ጥላቻና በቀል እንደሚዳርገን በማመዛዘን ወዲያውኑ ልንረሳው ወሰንን። ታዲያ በዚያን ምሽት አምርሬ ወደ እግዚአብሔር መጸለዬ አይረሳኝም። እንዲህም ስል ነበረ በመዳፈር ያነበነብኩት «አቤቱ አምላኪ ሆይ! አንተ በእውነት እስካለህና ለፍጡራንህ በጎነት የምታስብ እስከሆነ ሳትውል ሳታድር ከዚህ ከሕመሜ ፈውሰኝ! ከጓደኞቼም እኩል አድርገኝ! ይህም ካልተቻለ ሞቴን አፋጥንልኝ። በተረፈ ግን በዚህ መልኩ በሕይወት ብታቆየኝ አላመሰግንህም! አላከብርህም! አልወድህምም!» ስል እንቅልፍ ገርዝዞ ሊጥለኝ እስከሚቃረብ ተነዛነዝኩ። የሚገርመው ግን ለመጨረሻ ጊዜ ዓይኖቼን ከድኜ ባሸለብኩበት ወቅት ትዝ ያለኝ «እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን» የሚለው ጥቅስ ነበር።

ምዕራፍ ስድስት

ደግነቱ በዚያን ሰሞን ጓደኛዬ ዲያና ከጎኔ ተለይታ አታውቅም ነበር። ማንኛውንም ነገር ቢሆን እግዚአብሔር ለበጎ እንደሚያደርገው እንዳምንበት አበክራ ከማስገንዘብም ሌላ አንዳንድ ጥቅሶችን ከመጽሐፍ ቅዱስ በማንበብ ታበረታታኝ ነበር። በተለይም በሐኪሞቹ የሚለገሱኝን ምክሮች ተግባራዊ በማድረግ ከዚያ ከሆስፒታል ቶሎ የምወጣበትን ዘዴ ጭምር ባለማቋረጥ ትመክረኝ ነበር። እኔ ግን ዞሮ ዞሮ የሚታየኝ የዚያው የአካለ ስንኩልነቴ ጉዳይ ስለነበረ «ከሆስፒታል ብወጣስ ምን ጠቀሜታ ይኖረዋል? ያው ወላጆቼ ጋ ሄጄ እነርሱን ማስቸገር አይደለም?» በማለት ነበር የመለስኩላት።

«ለምን እንደዚህ ትያለሽ ጃኒ? መንገድሽን ሁሉ አደራ መስጠት ያለብሽ ለአንዱ ለእግዚአብሔር ብቻ ነው። ከዚህን መሰሉ አደጋ ላይ እንድትወድቂ ለምን እንዳደረገ ግልጽ እስከሚሆንልሽ ድረስ እምነትሽን በማጠናከር በትዕግሥት ልትጠባበቂ ይገባል።» ስትል ዲያና ፀጉሬን እያሻሸች መለሰችልኝ።

«እስከዚያስ ጊዜው እንዴት ያልፍልኛል? እንዲሁ አልጋ ላይ እንደተገላበጥኩ? ይህ እስከ መቼ ነው የሚሆነው?» ስል በምሬት ጠየቅኳት።

«አይዞሽ ጃኒ! ዋናው ነገር እግዚአብሔር ካንቺ ጋር መሆኑን እንድታምኚ እንጂ ሌላው ነገር ሁሉ ቀላል ነው። ጊዜው እንዴት ያልፍልኛል ላልሺውም መልሱ ቀላል ነው። ለምሳሌ ጊዜውን አንዳንድ ነገሮች በመጻፍና ሥዕሎችን በመንደፍ ልታሳልፊው ትችያለሽ።»

«ማን? እኔ?» ስል ከጮኽኩባት በኋላ፥ «ለመሆኑ እነዚህ የደነዘዙት ጣቶቼ ብዕሩንና ብሩሹን እንዴት ይዘውት ነው ለመጻፍም ሆነ ለመሳል የምችለው?» በማለት ጠየቋኳት።

«በጥርስሽ በመያዝ» አለችኝ በማበረታታት ፈገግ እያለች።

«በጥርሴ?» አልኩና ቃሉን ባለማመን ከደገምኩት በኋላ ዓይኖቼን ከብለል አድርጌ ከደንኳቸው። ከዚያም በአሳብ ጭልጥ ብዬ ነጎድኩ። «በቃ ዕድሜ ልኬን እንዲሁ ሽባ እንደሆንኩ ልቀር ነው?» ስል ብዙ ነገሮችን ማውጣትና ማውረዱን ተያያዝኩት። አዎን! እግዚአብሔር ለእኔ ያቀደውን በተግባር እስከሚያሳውቀኝ ድረስ በበኩሌም አንዳንድ ጥረቶችን ማድረግ እንደሚገባኝ አመንኩበት። በመሆኑም በወጌሻነት ሙያዋ በቅርብ ትረዳኝ የነበረችው አስታማሚዋ ክርስቲ ጠዋት ላይ ልትነበንኝ እንደመጣች ነበር። «እባክሽን የወደፊቱን ሕይወቴን በምመራበት በአንዳንድ መንገድ ብትረጂኝ?» ስል የጠየቅኳት።

«የምችለው ከሆነ በደስታ ነዋ የምረዳሽ! እስቲ ለማንኛውም ፍላጎትሽን በቅድሚያ ልወቀው?» ስትል መለሰችልኝ።

እኔም በጥርሴ አማካይነት የመጻፍና የመሣል ዕድሌን ልሞክረው መቁረጤን እንደነገርኳት ክርስቲ በደስታ እየተፍነከነከች፥ «ታዲያ ለዚህ ምን ችግር አለው? ዛሬውኑ ነው ማንኛውንም አስፈላጊ ነገር በማዘጋጀት ልምምዱን እንድትጀምሪ የማደርገው» ብላ በማበረታታት ትከሻዬን መታ አድርጋ ተለየችኝ።

በእርግጥም ክርስቲ በዚያኑ ዕለት ከሰዓት በኋላ ነበር አነስ ባለች አትሮንስ ላይ የተዘረጋጉ ወረቀቶችና የቀለም ብሩሾች ይዛ የመጣችው። ከዚያም ከአልጋ አውርዳ ከሚገፋው ጋሪ ላይ አመቻችታ በማስቀመጥ ቀለም የተነከረውን ብዕር በቅድሚያ እርሷው በጥርሶቿ በመያዝ ልምምዴን እንዴት መጀመር እንዳለብኝ አሳየችኝ።

ታዲያ ከብዙ ውጣውረድ ልፋትና ድካም በኋላ ነበረ ፊደሎችን ለመጻፍ የቻልኩት። በዚህም በተቀዳጀሁት አዲስ ዕድል በመጠቀም ለመጀመሪያ ጊዜ ለወላጆቼ ከሦስት መስመር ያልበለጠች ደብዳቤ ጻፍኩላቸው። ከእነርሱም በኩል የተለገሠኝ ማበረታቻና አድናቆት ከፍ ያለ ስለነበረ በልምምዴ እየገፋሁበት በመሄድ ከሦስት ወራት ባነሰ ጊዜ ውስጥ የማላላማ ጸሐፊ ሊወጣኝ ችሎ ነበረ።

ይሁን እንጂ ክርስቲ በጽሑፉ ብቻ ተገድቤ እንድቀር ባለመፈለጓ ወደ ሥዕል ነደፋው ደረጃም አሸጋገረችኝ። ይህንንም ቢሆን ለመለማመድና ውጤታማ ለመሆን ሳምንታት ባስቆጥርም ክርስቲን ሊያረካት የቻለው ግን የገና ካርዶች መሣሉን በጀመርኩበት ጊዜ ነው። አጅሪት ግን አሁንም ፋታ ባለመስጠት የጽሑፉንም ሆነ የሥዕሉን ልምምዴን ያለማቋረጥ እንድገፋበት ከሥር ሥሬ እንዳለች ነበር።

እንዳውም ይህም አንሶ የግሌ የፈጠራ ውጤቶች የሆኑ አንዳንድ ሥዕሎችን ጭምር እንዳዘጋጅ እስከማግባባት ደርሳ ነበር። እኔም ተስፋ አላስቆርጣትም በማለት በደህናው ጊዜዬ የጉብኝት ወቅት ያየኋቸውን አንዳንድ ተራራና ሸለቆዎች የባህር ዳርቻዎችና ሽንተረሮች እያስመሰልኩ መሳሉን ሆነ ብዬ ተያይዤው ነበር። በዚህም ረገድ ቢሆን የክርስቲን ልዩ አድናቆት ማትረፌ አልቀረም። ምክንያቱም ቀደም ሲል አባቴ የተለያዩ ሥዕሎችን ሲስል አይ ስለነበረ እንዳቅሜ አሁን መሳሉ አልከበደኝም።

በዚህን መሰሉ መንፈስ መጠመዴ ደግሞ የቀድሞውን ጭንቀቴን ለመዘንጋት አስችሎኛል። በአንድ ወቅት እራሴን ለመብላት፥ ለመተንፈስና ለመተኛት ብቻ እንደተፈጠረ ደካማ እንስሳ እንዳልቆጠርኩ ሁሉ ዛሬ ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋን ይግባውና

በእጇም ባይሆን በአፌ ብዕር ይዤ ለመጻፍ ከዚያም አልፎ ለመሣል በቅቼአለሁ።

እንደ እውነቱ ከዚያን በኋላ ነበረ እግዚአብሔር ለእኔ ያሰበው ልዩ ዕቅድ እንዳለ ወደማመኑ የተቃረብኩት። ለእንደ እኔ ብጤዎቹም አካል ጉዳተኞች አርአያ ወይም ምሳሌ ሊያደርገኝ በማለማመድ ላይ መሆኑንም የተገነዘብኩት በዚህ የፈተናዬ ወቅት ነበር። ከእንግዲህ ለሕይወቴ አንድ መመሪያ የመምረጡ ጉዳይ የእኔ ፋንታ ይሆናል። ይህንኑም ዝንባሌዬን በማስመልከት ለዳያና አጫውቻት ነበር። «እግዚአብሔር እንደ ሌሎቹ ቅዱሳን ባይገለጥልኝም ወይም ቃል በቃል ባያነጋግረኝም ዳሩ ግን በተዘዋዋሪ መንገድ ለአንድ ዓላማ እያዘጋጀኝ መሆኑን አምኜበታለሁ» በማለት ነበር የገለጽኩላት።

«እርሱ የለመኑትን የማይነሳ አምላክ ነውና የቀድሞውን ጸሎትሽን ሰምቶ እያሟላልሽ መሆኑን ነው በበኩሌ የማምነው» ስትል ነበረ በዚያን ጊዜ ዳያና የመለሰችልኝ። እኔም በዚህ አመላለሷ በመጠኑም ቢሆን ግራ በመጋባት

«የትኛውን የቀድሞውን ጸሎቴን እባክሽ?» ስል በአግርሞት ጠየቅኳት።

«ሕይወቴን ለውጠህ ለአንድ ለተቀደሰ ዓላማ እንድቆም አድርገኝ ስትይ ድሮ ትለምኚው የነበረውን ነዋ!» አለችና ዲያና መለሰችልኝ።

«አዎን!» ለዚያን መሰሉ አደጋ ከመጋለጤ በፊት ጌታዬን አዘውትሬ እጨቀጭቀው የነበረው አንድ ታዋቂ ወይም ዝነኛ ሰው እንዲያደርገኝ እንደነበረ ለዳያና ያጫወትኳት መሆኑ ትዝ ያለኝ በዚያን ጊዜ ነበር። ከዚህም በመነሣት ነበረ እኔም «እውነትሽን እኮ ነው ዳያና! ማን ያውቃል? እግዚአብሔር ለዚህ መሰሉ ሽባነት የዳረገኝ ምናልባት በእርሱ በኩል እንዳሟላው ያሰበው አንድ ዓላማ ቢኖረው ይሆናል ስል የመለስኩለት።

እንደዚህ ብዬ መመለሴ ደግሞ ኢምንት ታህል ሊያስደንቃት እንደማይችል ተሰምቶኛል። ምክንያቱም ጌታ ኢየሱስ እራሱ እንኳን ለተወሰነም ጊዜ ቢሆን በመስቀል ላይ በተሰቀለበት ወቅት ልክ እንደ እኔው እጅ እግሩ ደንዞ ለማላወስ እንደተሳነው ስለሚታወሳት ነው። ይሁን እንጂ የመስቀል ላይ ፈተናው እንዳከተመ እነኛ እጆችና እግሮች ተአምራትን ለማድረግ ተዘርግተውና ተራምደው ነበር። በመሆኑም ነው በዕብራውያን 4፡14–15 ላይ «እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፥ ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ። ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም» ተብሎ የተገለጸው በቀጥታ ለእንደ እኔ ዓይነቷ ምስኪን

መጽናኛ እንዲሆን የሰፈረ ለመሆኑ አምኜበታለሁ። እነሆም ጌታ ኢየሱስ ለአደጋ ከመጋለጤ በፊት ዕለት በዕለት በፊቴ ባይቆምም ቅሉ፥ አሁን ግን በነቃሁና ባሸለብኩ ቁጥር በዓይነ ሕሊናዬ ይታየኝ ነበር።

ከአሁን ወዲያ በመንፈስም ሆነ በአካል እራሴን በራሴ ላጠናክረው ብርቱ ጥረት አድርጌአለሁ። ባመቸኝ ጊዜ ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃላት ለመስማት በመጓጓቴ ከሥራ የማይለዩት ዳያናና እኅቴ ካቲ በመጡ ቁጥር እንዲያነቡልኝ አደርግ ነበር። ከዚያን በተረፈ ግን ጊዜዬን የማሳልፈው ከዚያ ከሚገኙ ጋሪ ላይ ተቀምጬ በጥርሶቼ በያዝኩት ብሩሽ አማካይነት አንዳንድ የመሰሉኝን ሥዕሎች በመሣጨር ነበር። የሚገርመው ደግሞ በዚህን መልኩ ከምስላቸው ሥዕሎች ሥር እንኳን ቢሆን አዲሱን ፊርማዬን ማስፈሬ ነው። ያም ፊርማዬ «እ.አ» የሚሉትን ምህፃረ ቃላት ያዘለ ሲሆን የሚያንጸባርቀውም «እግዚአብሔርን አመሰግኑ» የሚለውን ውስጣዊ እምነቴን ነበረ።

እንግዲህ እንዲህ በርታና ጠንክር ባልኩበት ጊዜ ነበረ ለሁለተኛ ጊዜ የገናን በዓል ለማክበር ወደ ወላጆቼ ቤት የተወሰድኩት። በዚያኑም አጋጣሚ ነበረ ወላጆቼ በካሊፎርኒያ ወደሚገኝ ወደ ሌላ የአካል ጉዳተኞች ሆስፒታል ሊያዛውሩኝ ማቀዳቸውን የገለጹልኝ። እኔም በዚህን መሰሉ ዕድል በጣም ብደሰትም ግን ወላጆቼን የማስከፍላቸው መሥዋዕትነት እየታሰበኝ ውስጥ ውስጡን መቆጨቴ አልቀረም። ታዲያ ከዚህ የትካዜ መንፈስ የተላቀቅኩት በመሃሉ ዲክ ሊጠይቀኝ በመምጣቱ ነው።

ከዚያን በኋላ ነገር ዓለሙን በመርሳት ከዲክ ጋር ልክ እንደ ጤነኛ ልጃገረድ ስሽሞነሞን ከረምኩ። ንጽሕናዬን መጠበቁና አለባበሴን ማሳመሩ ሁሉ የዕለት ተግባሬ ሆነ። እንደ ዱሮውም ከፊት ለፊቴ መስታወት እንዳይለይ፥ ፀጉሬን እንዲያበጥሩኝ፥ ፊቴን እንዲወለውሉኝና ከንፈሬን ቀለም እንዲቀቡኝ ማድረጉን ሆን ብዬ ተያያዝኩት። ሌላው ቀርቶ ከዲክ ጎን ተቀምጬ በመኪና መንሸራሸሩን ሁሉ ተለማምጄው ነበር። ዳሩ ግን ምን ያደርጋል የዕረፍቱ ጊዜ አልቆ ዲክ ወደ ኮሌጁ ተመልሶ ሄደ። ያም ለጥቂት ቀናት ያህል የተለማመድኩት መተቃቀፍና መሳሳም ሁሉ እንደ ሕልም ሆኖ አለፈ። ከዚያም በላይ ደግሞ ወላጆቼ ወደ አመቻቹልኝ ወደ አዲሱ የካሊፎርኒያ ሆስፒታል መጓዝ ነበረብኝ። ደግነቱ ግን በካሊፎርኒያው ጉዞዬም ሆነ ቆይታዬ ትልቁ እኅቴ ጄይ ከጎኔ እንዳትለይ በመደረጉ ሞንቀቱ በመጠኑም ቢሆን ተቀንሶልኝ ነበር።

ምዕራፍ ሰባት

ወደ ካሊፎርኒያ የበረርነው በአውሮፕላን ነበር። ታዲያ በዚያን ጊዜ ሁሉ የሚታየኝ ከአዲሱ ሆስፒታል ቶሎ ደርሼ በሐኪሞቹ እርዳታ ቢያንስ ከእጆቼ ሽባነት እንደምላቀቅ ነበር። ይህኛው ጉጉቴ ከተሟላልኝ ደግሞ ከዲክ ጋር ወደፊት የምንመሠርተው ትዳርና የምናሳልፈው የፍቅር ሕይወት እየታየኝ ውስጥ ውስጡን በደስታ ታምሼአለሁ። የካሊፎርኒያው ሆስፒታል እንደ ግሪን ኦክሱ ሆስፒታል ለዓይን የሚከብድ አልነበረም። ከግቢው ውበት በተጨማሪ የአስታማሚዎቹም ቅልጥፍናና ትብብር የሚደነቅ ሆኖ ነው ያገኘሁት። በዚህ ላይ ደግሞ ወላጆቼ ሆስፒታሉን መላመድ አለመላመዴን በዓይናቸው ለማየት ሲሉ ወደዚያ መጥተው ውለው በማደራቸው ከምንጊዜውም ይልቅ ቅልል ብሎኝ ነበረ የከረምኩት።

ራንቾ በሚባለው በአሁኑ ሆስፒታል ውስጥ ገና ከመድረሴ አንሥቶ ልዩ እንክብካቤና እርዳታ ተደርጎልኝ ነበር። በተለይም ደግሞ ከንዶቼን ለማንቀሳቀስ የምችልባቸው የተለያዩ ዘዴዎችን ተግባራዊ ለማድረግ በበኩሌም ብርቱ ጥረት በማድረጌ በጥቂት ቀናት ውስጥ ነበረ መላወስ የጀመሩልኝ እንደ አጋጣሚም ሆኖ ደግሞ በቅርብ እንዲረዳኝ የተመደበልኝ ሐኪም የተለየ እንክብካቤና ጥንቃቄ ያደርግልኝ ነበር። በመሆኑም ከቀኝ ክንዴ መዳፍ ቋንጃ ጋር በልዩ ዘዴ ባጋጠመልኝ ሹካ አማካይነት እራሴን በራሴ ለመመገብ እንኳን ችዬ ነበር። ያም ሆኖ ግን አጠቃቀሙን በአግባቡ እስከምካንበት ድረስ ወደ አፌ ከምለው ይልቅ ተዝረከርኮ የሚወድቀው ምግብ ይበልጥ ነበር። ይህም አንሶ ደግሞ ወር ባልሞላው ጊዜ አሁንም እራሴን በመቻል የምዘዋወርበትን ጋሪ ማሽከርከር ጀምሬ ነበር። እርግጥ በልምምድ መሀል ከግርግዳ መላተሜም ሆነ አልፎ አልፎም አንዳንድ በኮሪደሩ ላይ የሚተላለፉትን አስታማሚዎችን መግጨቴ አልቀረም። ምክንያቱም የጋሪውን መሪ የምቆጣጠረው ልክ እንደ ምግብ ሹካው ሁሉ ከመዳፉ ቋንጃዬ ጋር በተገጠመ መሣሪያ አማካይነት በመሆኑ ነው። እንግዲህ ይህን መሳዩን ጥበብ በመካን ነበረ በካሊፎርኒያው የራንቾ ሆስፒታል ለሦስት ወራት ያህል የቆየሁት።

ትዝ ይለኛል በሚያዚያ ወር አጋማሽ ላይ በ1969 ዓ.ም ነበረ ከሆስፒታሉ ወጥቼ ወደ ቤቴ እንደምወስድ የተነገረኝ። እኔም በዚህን መሰሉ ዱብ ዕዳ በመደናገጥ ከዶክተሩ ጋር አተካራ መግጠሜ አልቀረም።

«ዶክተር የእኔ ተስፋና ምኞት ብሎም ይህን ያህል መፍጨርጨር እኮ አንድ ቀን ቢያንስ እጆቼን ለማንቀሳቀስ ታስችሉኝ ይሆናል

በማለት ነበር። ታዲያ አሁን ወደ ቤትሽ መመለስ አለብሽ የምትሉኝ ተስፋ በመቁረጣችሁ ነው?» ስል ጠየቅሁት።

«አዎን ጃኒ! እጆችሽንና ጣቶችሽን ለምንጊዜም ቢሆን ልታላውሺያቸው እንደማትችዪ ነው የደመደምነው። ስለዚህ እዚህ በመቆየት የምታገኚው ጠቀሜታ ስለሌለ ወደ ቤት እንድትመለሺ ወስነናል። የአንቺ እዚህ መቆየት ወላጆችሽ ገንዘባቸውን በከንቱ እንዲያፈስሱ ከመጋበዝ በስተቀር የሚያስገኘው ትርፍ የለም። ስለዚህ አንቺም ቁርጡን በማወቅ ወደ ቤት ተመልሰሽ ባለሽ አቅም ሁሉ አዲስ ሕይወት ለመምራት መዘጋጀትና መነሣሣት አለብሽ» ሲል ዶክተሩ የመጨረሻውን መርዶዬን ነገሮኝ አረፈው። እውነቱን ለመናገር እነኚህን መሰሎቹን ተስፋ አስቆራጭ ቃላት እሰማቸዋለሁ የሚል ጥርጣሬ አልነበረኝም። ጸሎቴም ሁሉ አንድ ቀን ብሩህ ተስፋ እቀዳጅ ይሆናል በሚል ምኞት የታገዘ ነበር። ሆኖም አሁን ምንም የማያወላዳውን የዶክተሮቹን ውሳኔ ሰማሁ። ከእንግዲህ ማለትም እስከ ዕድሜዬ ማብቂያ ድረስ የሌሎችን እርዳታ ጠያቂ! ጠባቂ! ሆኜ መቅረቴ ነው ማለት ነው።

በዚያኑ ይህን መርዶ በሰማሁበት ዕለት ምሽት ነበረ በጥርሶቼ በያዝኩት ብዕር አማካይነት የሚከተለውን ቆራጥ ደብዳቤ ለፍቅረኛዬ ለዲክ የጻፍኩለት፦

«የማፈቅርህ ዲክ፥

እነሆ፥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን ቀርቶ ለተቀረው ሕይወቴ ሁሉ እጆቼንም ጭምር ላላውሳቸው እንደማልችል በዛሬው ዕለት በሐኪሞቼ ተነግሮኛል። በሌላ አነጋገር የተቀረውን ዕድሜዬን ሁሉ የምገፋው በሰዎች እገዛና እርዳታ ይሆናል ማለት ነው። ይህም ማለት ከወንድ ጋር ትዳር መሥርቼ የሚስትነት ወጉን ላሟላ አልችልም ማለት ነው። ስለዚህ እኔ እንደማፈቅርህ ሁሉ አንተም እንደምታፈቅረኝ ባውቀውም ለባልና ሚስትነት የመተሳሰባችን ጉዳይ ግን አከትሞለታል። እግዚአብሔር ለአንተ የመረጠልህ ሌላ የትዳር ጓደኛ ስላለች በዚያ ልትጽናና ይገባል። እኔ ግን ያለኝ አማራጭ የብቸኝነት ሕይወትን መምራት ብቻ ነው። እናም ከዚህ በማስከተል ውድ ፍቅረኛዬን የማላስብህ ይህ ደብዳቤ ከደረሰህ ዕለት አንሥቶ የምትሰማማህን ልጅ እንድታፈላልግ ነው። በተረፈ ግን የአንተና የእኔ የእኅትና የወንድምነት ግንኙነት እንደሚቀጥል ባለሙሉ ተስፋ ነኝ።»

ደብዳቤውን ጽፌ እንደጨረስኩ ከሥሩ እንደ ልማዴ «ያንተው ጃኒ» የሚሉትን ቃላት አላሳረፍኩበትም። በምትኩ «ጃኒ» ብቻ ብዬ ነበረ የጻፍኩት።

የዚያን ሌሊቱ አስተዳደሬ ከምንጊዜውም ለየት ያለ ነበረ። ከዲክ ጋር ያሳለፍኳቸውን ትዝታዎች ደረጃ በደረጃ በማስታወስ እንዳለቀስኩና እንደ ተንሰቀሰቅሁ ነበረ ወለል ያለው። የእኔ ተስፋ ቢያንስ እጆቼን በማንቀሳቀስ ምግብ የማብሰል፥ መኪና የመንዳት፥ ብሎም ከፍቅረኛዬ ጋር የመተቃቀፍና የመተሻሸት ዕድሉ ይኖረኛል የሚል ነበረ። በዚያኑም መጠን በገዛ እጄ ገላዬን የመተጣጠብ፥ ፀጉሬን የማበጠር፥ ፊቴን የማሰማመርና ዓይኖቼን የመኳኳል ችሎታውን እቀዳጅ ይሆናል የሚል ነበረ። ይህንን የመሳሰሉትን ቀላል ግዳጆች የሚያሟሉ ሴቶች ደግሞ የሞቀ ትዳር ይዘው መውለድ መከበዳቸውን በዓይኔ ጭምር ያየሁት ነው። የእኔው ግን ከማናቸውም የባሰ ሆነና ይኸው ከብቸኛው ፍቅረኛዬ ከዲክ እንኳን ጋር አለያየኝ። አዎን ዲክ ከእኔ ከአካለ ጥምልምሏ ጋር ተጋብቶ ዕድሜ ልኩን ሲሠቃይና ሲዘበትበት መኖር የለበትም!!!

ምዕራፍ ስምንት

ከካሊፎርኒያው የራንቾ ሆስፒታል እንድወጣ ተደርጎ ወደ ቤት በተመለስኩበት ጊዜ በአእምሮዬ ውስጥ መላልሶ ይደውል የነበረው የሮሜ 8፡28 መልእክት ነበር። መቼም ጳውሎስን የመሰለ ብዙ ፈተና የደረሰበትና በአያሌ ውጣ ውረዶች መካከል ያለፈ ሐዋርያ «እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን» ሲል መጻፉ በመጨረሻ ላይ ድልን እንደሚቀዳጅ በመተማመኑ ነው ስል እኔም ተጽናንቼ ነበር።

አሁንም ቢሆን በአመዛኙ ከጎኔ የማትለየው ዲያና ደግሞ ሌላም የመጽናኛዬ ምንጭ ነበረች። እንዳውም አንድ ቀን «ትሰሚኛለሽ ጃኒ ምንም እንኳ የራንቾ ሐኪሞች ከእንግዲህ እግርና እጅሽን የማላወስ ተስፋ እንደሌለሽ ቢገልጹልሽም፥ የእነርሱን ቃል አሜን ብለሽ በመቀበል ተስፋ መቁረጥ የለብሽም» ስትል ተናገረችኝ።

«ሌላ ምን አማራጭ አለኝ ብለሽ ነው?» በማለት ጠየቅኋት።

«ያለሽ አማራጭ በተረፈው ጤናማ በሆነው የአካላት ክፍልሽ መጠቀም ነዋ!» ስትል መለሰችልኝ። «ለምሳሌ?» ስል ማብራሪያ በመፈለግ ጠየቅኳት።

«ለምሳሌ በአዕምሮሽ፥ በድምፅሽ፥ በዓይኖችሽና በጆሮችሽ። እነኚህን ሁሉ ካሠራሻቸው ፍሬያማ እንደምትሆኚ ማመን አለብሽ። ምክንያቱም ብዙ ካንቺ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የአካል ጉድለት ያላቸው ሰዎች በብርቱ ጥረታቸው ታሪክ ትተው ለማለፍ መቻላቸው ነው!» አለችና ፈገግ እያለች አየችኝ። እኔም አፀፋውን እየመለስኩላት «እስቲ ወደፊት እናያለና!» ስል አሾፍኩባት።

ዲክ በዚያኑ ሰሞን ሊጠይቀኝ መጥቶ ነበር። እርግጥ ለጻፍኩለት ለዚያ ቁርጠኛ ደብዳቤ መልስ ባይጽፍልኝም እንኳ፥ አሁንም ቢሆን እኔን የማግባት ፍላጎት እንዳለው ገለጸልኝ። «አየሽ አንቺን ማግባት ማለት ዕድለኛ መሆን ማለት ነው። ስለ ምን ከጋሪ ላይ የማትወርድ ልጃገረድ በማግባቱ ሪገድ እኔ የመጀመሪያው ሰው ስለምሆን ነው» ሲል ነበር ሊያሳምነኝ የሞከረው። እኔ ግን በዚህ አቀራረቡ ቅሬታ ገብቶኝ «ለታሪክ ስትል ነዋ የምታገባኝ?» በማለት ጠየቅሁት።

«ለታሪክነቱ ሳይሆን እንደተለየ የእግዚአብሔር ስጦታም አድርጌ ስለምቆጥረው እንጂ» አለና መለሰልኝ።

«የእግዚአብሔር ስጦታ ነው ያልከው! እንደ እውነቱስ ከሆነ ማናቸውም የእግዚአብሔር ስጦታ ሁሉ የተባረከ ነው፤ ግን እንደ እኔ ዓይነቷን አካል ጉዳተኛ የሚጨምር አይደለም።»

«አካል ጉዳተኛ ብትሆኚም እኮ ተረዳድተን መኖር እንችላለን።»

«አሁን የምታወራው ሁሉ ሕልማዊ ቅዠትና ከተጨባጭ ሁኔታ በጣም የራቀ ነው። ትዳር አብሮ መብላት መጠጣት ብቻ ሳይሆን፥ ሌሎችንም ብዙ ኃላፊነቶች የመጋራት ልምድን ያካተተ መሆኑን ለምን ትዘነጋዋለህ?» ስል ላጽናናው ፈገግ አልኩ።

ለዚህ አባባሉ ዲክ መልስ አልሰጠኝም። በፀጥታ እንደ ተዋጠ ለብዙ ጊዜ አቀርቅሮ ከቆየ በኋላ በመጨረሻ ላይ ተሰናብቶኝ ወጣ።

ከዚያን ዕለት በኋላ ዲክ ከአንዳንድ ልጃገረዶች ጋር የመታየቱ ወሬ ቀስ በቀስ ሊደርሰኝ ጀምሮ ነበር። ያም ሆኖ ግን ውስጥ ውስጡን ከመታመስ በስተቀር ምንም ነገር ለማድረግ አልችልም ነበር። በመሆኑም እንደ ምንም በመጨከንና እራሴን በማጽናናት ለመበረታታ ቻልኩ።

ውሎ ባደረ መጠን ደግሞ ሌሎች ተደራራቢ ቅሬታዎች ሳያድሩብኝ አልቀረም። በዚያ ቤት ውስጥ ተወልጄ እንዳላደግኩበት፥ እንዳልቦረቅኩበትና እንዳልጨፈርኩበት አሁን ባለፉ ትዝታዎች ብቻ ተጠምጄ የመቅረቴና ቀኑን ሙሉ ብቻዬን በአሳብ ስቆዝም የመዋሌ ነገር በአሳቤ እየተመላለሰ ሰላም ነስቶኝ ነበር። ለዚህም ነው አባቴ የሁኔታዬን መለዋወጥ በማየት «ጃኒ ለምንድን ነው ብዙ ጊዜ ተከዘሽ የማይሽ?» ሲል የጠየቀኝ።

«እኔ እንጃ! እንደው ፋይዳ ቢስ ሆኜ የመቅረቴ ነገር ውስጥ ውስጡን እየበላኝ ይሆናላ» አልኩት እንባዬ በዓይኖቼ እያቆረዘዘ።

«አይዞሽ ጃኒ! ሰው እኮ ፍሬያማ የሚሆነው በእጆቹ ስለሠራባቸውና በእግሮቹ ከስፍራ ስፍራ ስለተዘዋወረ ብቻ አይደለም። መንፈሰ ብርቱ ሆኖ ለጎብረተሰቡ ሊያበረክታቸው የሚችላቸው ሌሎችም አስተዋጽኦዎች አሉ። ለምሳሌ በምክር አለጋገሱ፥ በሃይማኖት ጽናቱ፥ በአስተሳሰብ ጥልቀቱና በመሳለለው። ስለዚህ እነኚህ መሰሎቹን ጸጋዎች የምንላበሰው በእጃችን በመሥራት ሳይሆን በአዕምሮአችን ምጥቀት ብቻ መሆኑን በመረዳት አንቺም በዚህ መስመር ልትሰለፊ ትችያለሽ።»

«አሁን ያልከው ልክ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ቅር የሚለኝ ነገር ለምን እግዚአብሔር በዚህ አፍላ ዕድሜዬ አሽመድምዶ

አስቀረኝ? ለምን ለጥቂት ዓመታት እንኳን አይታገሰኝም ነበር? ከማለት የመነጨ ነው። ደግሞስ ለዚህ መሰሉ አደጋ የተዳረግሁት ምን ኃጢአት ብሠራ ነው? ስል እራሴን አስጨንቀዋለሁ።»

«አይ ጃኒ! ምን ኃጢአት ብሠራ ነው አልሽ? ኃጢአታችንንማ አንድ ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሸከሞልን ነፃ አውጥቶናል። እና በአንቺ ላይ ይህን መሰሉ አደጋ መድረሱ ለሌላ ዓላማ ይሆናል እንጂ ኃጢአት በመሥራትሽ አይደለም» አለኝ አባቴ በእርግጠኝነት።

አዎን! አባቴ እንዳለው ሁሉ ባለፉት ዘመናቴ የሠራኋቸውን ኃጢአቶች ሁሉ ክርስቶስ ደምስሶልኛል። እናም በዚህ ሙሉ በሙሉ ልጽናና ይገባል። ይሁን እንጂ ይህን እያወቅሁ ደግሞ አሁንም እራሴን ለሌላ ኃጢአት ማጋለጥ የለብኝም። በእግዚአብሔር ጥበብ ውስጥ ገብቼ ለምን እንደዚህ አደረግከኝ ብዬ ማማረርና ማጉረምረም የለብኝም። ኃጢአት በተግባር የሚገለጸው ድርጊት ብቻ ሳይሆን ሕሊናዊ ጥርጣሬና ዓመጽንም ያካትታል። በዚህን መሰሉም አስተሳሰብ መጠመድ ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 8፡7–8 ላይ «ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፥ መገዛትም ተስኖታል፤ በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም» ሲል ያስተላለፈልንን ምክር ተግባራዊ አለማድረግ መሆኑን ተረዳሁት።

ከዚህም በመነሣት ነበር በቁርጠኝነት «አቤቱ ጌታዬ ሆይ! ስለ አለፈው በደሌ ይቅር በለኝ። የጥርጥርን መንፈስ ከእኔ አርቅ። የአልጋ ቁራኛ እንድሆን ፈቃድህ ቢሆንም ይህንን ለአንድ ዓላማ እንዳደረግከው በማመን እንድጽናና እርዳኝ። በቀሪው ሕይወቴ አንተን አገለግል ዘንድ ለበጎና ለተቀደሰ ምግባር አነሣሣኝ፥ ምራኝም!» ስል ጸለይኩ።